የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፩

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.33
ADDIS ABABA 7th March, 2019

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፫/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ገጽ……………….ገጽ፲፩ሺ፮

**Content**

Proclamation No. 1113/2019

Organizations of Civil Societies Proclamation………..…Page 11006

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፫/፪ሺ፲፩

## የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠውን የመደራጀት መብት በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የመደራጀት መብት በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ ሌሎች መብቶችን ለማስከበር ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ፤

በሕገ መንግሥቱ እንደተደነገገው፣ የመንግሥት አሠራር በግልጽነት፣በተጠያቂነትና በአሳታፊነት እንዲከናወን ለማድረግ የነቃና በነፃነት የተደራጀ ማኅበረሰብ መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በአገሪቱ ልማትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያላቸው ሚና እንዲጎለብት ለማድረግ የተመቻቸ ምህዳር መፍጠር ወሳኝ መሆኑን በመረዳት፤

## PROCLAMATION NO.1113/2019

## ORGANIZATIONS OF CIVIL SOCIEITIES PROCLAMATION

**WHEREAS,** it is found necessary to enact a law to give full effect to the freedom of association enshrined in the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia as well as International human rights instruments ratified by Ethiopia;

**RECOGNIZING** ,the instrumental role of freedom of association for the full exercise of other rights recognized in our Constitution;

**FIRMLY CONVINCED,** that the existence of an active and freely organized society is imperative to ensure that government affairs are conducted in a transparent, accountable and participatory manner;

**REALIZING** ,that the creation of an enabling environment is essential to enhance the role of civil society organizations in the development and democratization of the country;

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ተጠያቂነት እና የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ድርጅቶቹ ሥራቸውን በሕግ መሠረት መሥራታቸውን መቆጣጠር በማስፈለጉ፤

በሕብረተሰቡ ዘንድ የበጎ አድራጎት እና የበጎ ፈቃደኝነት ባሕልና እንዲዳብር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ የነበሩበትን ክፍተቶች ለመሸፈን የሚያስችል አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፲፫/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "**የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት**" (ከዚህ በኋላ **ድርጅት** ተብሎ የሚጠራ) ማለት ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች በፈቃደኝነት የሚመሠረት፣ የመንግሥት አካል ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ያልወገነ እና ሕጋዊ ዓላማን ለማሳካት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አካል ሲሆን፣የሙያ ማኅበራትን፤የብዙኀን ማህበራት እና የድርጅቶች ኅብረቶችን ይጨምራል።

**RECOGNIZING,** the need to regulate civil society organizations to ensure accountability and maximum public benefit from the sector;

**COGNIZANT OF,** the importance of nurturing the culture of volunteerism and charity in the society;

**WHEREAS,** it is found necessary to enact a new law to address the shortcomings of the Charities and Societies Proclamation 621/2009, which was in force prior to the issuance of this Proclamation;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55/1 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## SECTION ONE
## GENERAL

### 1/ Short Title

This Proclamation may be cited as the "Organizations Of Civil Societies Proclamation No.1113/2019".

### 2/ Definitions

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1/ "Organizations Of Civil Societes" (hereafter called 'Organization') means a non-governmental, non-partisan entity established at least by two or more persons on voluntary basis and registered to carry out any lawful purpose, and includes non-government organizations, professional associations, mass based societies and consortiums;

፪/ “**አገር በቀል ድርጅት**” ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ሕጋዊ ሥራን ለመሥራት በዚህ ሕግ መሠረት በኢትዮጵያውያን፣ በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነ የውጭ አገር ዜጎች ወይም በሁለቱ አማካኝነት በጋራ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

፫/ “**የውጭ ድርጅት**” ማለት በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመና በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው።

፬/ "**የበጎ አድራጎት ድርጅት**" ማለት ለጠቅላላው ህዝብ ወይም ለሶስተኛ ወገን መስራትን አላማ አድርጎ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

፭/“**የሙያ ማኅበር**” ማለት አንድን ሙያ መሠረት በማድረግ የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን፣ ዓላማውም የአባላቱን መብትና ጥቅም ማስከበር፣ የሙያ ሥነ-ምግባርን ማሳደግ፣ የአባላትን አቅም መገንባት እንዲሁም በሙያቸው ለሕዝብና ለአገር አስተዋጽዖ ማድረግን የሚጨምር ነው።

፮/ “**ኅብረት**” ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ድርጅቶች የሚቋቋም ስብስብ ሲሆን፣ የኅብረት ኅብረቶችን ይጨምራል።

፯/ “**ቦርድ**” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ቦርድ ነው።

፰/“**የዘርፍ አስተዳዳሪ**” ማለት የተለየ ፈቃድ በሚያስፈልጋቸው የሥራ ዘርፎች ለሚሰማሩ ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥ እና ተገቢውን ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ነው።

፱/ “**ልዩ ፍቃድ** ማለት በአንድ ስራ ላይ ለመሰማራት በህግ ፍቃድ እንደሚያስፈልግ የተገለጸ በሆነ ጊዜ በዚህ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚሰጥ የፈቃድ አይነት ነው፡፡

2/ “Local Organization” means a civil society organization formed under the laws of Ethiopia by Ethiopians, foreigners resident in Ethiopia or both;

3/ “Foreign organization” means a non-governmental organization formed under the laws of foreign countries and registered to operate in Ethiopia.

4/ “Charity organization” means an organization established with the aim of working for the interest of general public or third party.

5/ “Professional association” means an organization formed on the basis of a profession, and its objectives may include protecting the rights and interests of its members; promoting professional conduct, building the capacities of members or mobilize professional contributions of its membership to the community and the country;

6/ “Consortium” means a grouping formed by two or more civil society organizations, and includes consortia of consortiums;

7/ “Board” means the Civil Society Organizations Board established in accordance with the provisions of this Proclamation;

8/ “Sector administrator” means a government body mandated to issue licenses for organizations operating in sectors that require special licensing and to provide appropriate technical follow up and support;

9/ “Special License” means a license given to participat on certain activity when prescribed by law.

፲/ **“ኤጀንሲ”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ነው።

10/ “Agency” means the Civil Society Organizations Agency established in accordance with the provisions of this Proclamation;

፲፩/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ክልል ነው።

11/ “State” shall mean a State specified under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia as a member of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

፲፪/ **“ምክር ቤት”** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፭ መሠረት የሚቋቋመው የድርጅቶች ምክር ቤት ነው።

12/ “Council” means a grouping of civil society organizations formed in accordance with Article 85 of this Proclamation;

፲፫/ **“የሃይማኖት ተቋም”** ማለት የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማደራጀትና ለማስፋፋት የሚያቋቁሙት ተቋም ሲሆን የበጎ አድራጎት ዓላማዎችን ለማሳካት የተቋቋሙ ወይም የኃይማኖት ተቋሙ የሚያቋቁማቸውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን አይጨምርም።

13/ “Religious institution” means an institution established by believers to organize and propagate their religion and shall not include organizations established by the religious institutions to advance charitable purposes.it doesnot not include an organization organized by the religious institution;

፲፬ **“የራስ አስተዳደር”** ማለት ድርጅቶች በምክር ቤቱ አማካኝነት ራሳቸውን ለማስተዳደር በፈቃዳቸው በሚያወጡት የሥነ ምግባር ደንብ የሚመራ አስገዳጅ የቁጥጥር ሥርዓት ነው።

14/ “Self-regulation” means a mandatory regulatory system led by a voluntary code of conduct adopted by Organizations through the Council to govern themselves;

፲፭/ **“የሥራ አመራር አባላት”** ማለት ተጠሪነታቸው ለድርጅቱ የበላይ አካል (እንደሁኔታው ለድርጅቱ ጠቅላላ ጉባዔ ወይም ቦርድ) ሆኖ የድርጅቱን የሥራ ሂደት እንዲከታተሉና እንዲቆጣጠሩ በድርጅቱ አባላት ወይም በድርጅቱ ቦርድ የተመረጡ ሰዎች ናቸው።

15/ “Members of Management” means persons elected by members or the board of a civil society organization to manage and follow up the operations of the organization and accountable to the highest body of the organization (the General Assembly or Board as appropriate);

፲፮/ **“የሥራ መሪ”** ማለት የድርጅቱን የዕለት ከዕለት ሥራ በበላይነት እንዲመራ በውል የተቀጠረና ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ለድርጅቱ ቦርድ የሆነ ግለሰብ ነው።

16/ “Officer” means a person hired to manage the day to day operations of the organization and accountable to the management committee or Board of the organization;

፲፯/ **“ሰው”** ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው።

17/ “Person” shall mean any physical or juridical person;

፲፰/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ድንጋጌ የሴት ፆታንም ያካትታል።

18/ Any expression in the masculine gender in this Proclamation includes the feminine.

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

፩/ ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፦

ሀ) በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች፣

ለ) በውጭ ድርጅቶች፣

ሐ) በውጭ አገር በሚንቀሳቀሱ፣ክፍለ አህጉራዊ፣አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ዓላማን ለመተግበር በተቋቋሙ አገር-በቀል ድርጅቶች፣

መ) በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች፣

ሠ) የሃይማኖት ተቋማት በሚያቋቁሟቸው በጎ አድራጎት ድርጅቶች፤

፪/ ለዚህ አንቀፅ አላማ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚንቀሳቀስ ድርጅት ማለት የተቋቋመበትን ዋና ስራ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚሰራ ፣ ቋሚ የሆነ ቢሮ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች ከፍቶ የሚንቀሳቀስ፣ ቋሚ የሆኑ አባላት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች አፍርቶ የሚንቀሳቀስ ወይም የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ ቋሚ በሆነ መንገድ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡

፫/ ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ) በሃይማኖት ተቋማት፣

ለ) በእድር፣ እቁብና መሰል ባሕላዊ ስብስቦች፣

ሐ) በሌላ ሕግ መሠረት በተቋቋሙ ተቋማት።

**ክፍል ሁለት**

**የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ**

**፬/ መቋቋም**

፩/ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ “ኤጀንሲ” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

**3 / Scope of Application**

1/ This Proclamation shall be applicable to:

a) Organizations operating in two or more regional states;

b) Foreign organizations;

c) Organizations established in Ethiopia to work on international, regional or sub regional issues or not operate abroad;

d) Organizations operating in the City Administration of Addis Ababa or Dire Dawa; and,

e) Charitable organizations established by religious institutions.

2/ For the purpose of this provision Organizations operating in two or more regional states means an organization which implement its main mission in two or more regional states, an organization which have its permanent office in two or more regional states, an organization which have permanent members and operate in two or more regional states or an organization which collects fund in two or more regional states permanently.

3/ This Proclamation shall not be applicable to:

a) Religious institutions;

b) Edir, Equb and similar traditional institutions

c) Organizations formed under other laws.

**SECTION TWO**

**CIVIL SOCIETY ORGANIZATION AGENCY**

**4/ Establishment**

a. Ageny for Civil Societies Organizations Proclamation (hereinafter referred to as the “Agency”) is hereby established by this Proclamation with its own legal personality and as an institution of the Federal Government.

፪/ የኤጀንሲው ተጠሪነት ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ይሆናል።

**፭. <u>የኤጀንሲው ዓላማዎች</u>**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥትና ኢትዮጵያ ፈርማ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የመደራጀት መብት በተሟላ ሁኔታ እንዲረጋገጥ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤

፪/ ድርጅቶች በተመዘገቡበት ዓላማ መሠረት ሥራቸውን ማከናወናቸውን በመከታተልና በመቆጣጠር የሕብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

፫/ ድርጅቶች አቅማቸው እንዲጎለብትና ተልዕኮአቸውን በብቃት እንዲወጡ ማስቻል፤

፬/ በኅብረተሰቡ ዘንድ የበጎ አድራጎት እና በጎ ፈቃደኝነት ባሕል እንዲዳብር ማድረግ፤

፭/ ድርጅቶች አሳታፊ የሆነ፣ ግልጽነትና እና ተጠያቂነት የሠፈነበት የውስጥ አስተዳደር እና አሰራር እንዲኖራቸው ማበረታታትና መደገፍ፤

፮/ በድርጅቶችና በመንግሥት መካከል ሊኖር የሚገባውን መልካም የሥራ ግንኙነት ሊያጠናክሩ የሚችሉ አሰራሮችን መዘርጋት፤

፯/ ለድርጅቶች የራስ ቁጥጥርና አስተዳደር ስርዓት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡

**፮/ <u>የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት</u>**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ድርጅቶችን መመዝገብ፣ መደገፍ፣ ሥራቸውን ማሳለጥና ማስተባበር፤

፪/ ድርጅቶች ሥራቸውን በሕግ አግባብ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤

b. The Agency shall be accountable to the Federal Attorney General.

**5/ <u>Objectives of the Agency</u>**

The Agency shall have the following objectives:

1/ Create conducive environment for the full exercise of freedom of association in accordance with the stipulations of the FDRE Constitution and international agreements ratified by Ethiopia;

2/ Ensure maximum public benefit by supervising whether organizations carry on their activities in accordance with their registered objectives;

3/ Build the capacity of organizations to enable them to accomplish their objectives effectively;

4/ Foster the culture of philanthropy and volunteerism in the society;

5/ Encourage and support organizations to make sure that they have internal governance systems which ensure transparency, accountability and participation;

6/ Put in place mechanisms to strengthen positive working relations between organizations and the government;

7/ Support the civil society organization self-regulation and self administration system.

**6/ <u>Powers and Functions of the Agency</u>**

The Agency shall have the following powers and functions:

1. Register organizations and support, facilitate and coordinate their activities in accordance with this Proclamation;
2. Monitor and supervise organizations to ensure that they undertake their activities in compliance with the law;

፫/ የድርጅቶችን ዓመታዊ የሥራና የገንዘብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በዚህ ሕግ በተወሰነው መሠረት መመርመር፣

፬/ ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የውስጥ አስተዳደር እና የራስ አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠትና ተፈፃሚነቱን መከታተል፣

፭/ ከሚመለከታቸው የክልል መንግስታት አካላት ጋር በመተባበር በአገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን ቁጥር፣ የተሰማሩባቸውን ክልሎችና የሥራ ዘርፎች፣ የተጠቃሚዎቻቸውን እና የአባሎቻቸውን ብዛት እና መሰል መረጃዎች የሚይዝ የመረጃ ማዕከል ማቋቋም እንዲሁም እነዚህን መረጃዎች መተንተንና በጋዜጣና በድረ-ገጽ አሳትሞ ማሰራጨት፣

፮/ ከፌደራልና ከክልል የመንግሥት አካላት እንዲሁም ከድርጅቶች ጋር ቋሚ የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣

፯/ ኃላፊነቱን ለመወጣት ከዘርፍ አስተዳዳሪዎች ጋር በትብብር መሥራት፣

፰/ ድርጅቶች መንግሥት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ሕጎች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት፣

፱/ ድርጅቶች በአገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፣ሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ እና የልማት እንቅስቃሴ ያላቸውን ሚና አስመልክቶ ተገቢውን ጥናት ማካሄድና መንግሥትን ማማከር፣

፲/ ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው የልማት ሥራዎች መንግሥት ከሚያወጣቸው የልማት ዕቅዶች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ የሚያግዙ የፖሊሲ መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣

፲፩/ አግባብነት ባላቸው ሕጎች ስለሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የድርጅቶችን መተዳደሪያ ደንቦችና ማሻሻያዎቻቸውን ማረጋገጥና መመዝገብ፣

3. Examine and the annual activity and financial reports of organizations conduct the necessary follow up in accordance with the stipulations under this Proclamation;

4. To provide the necessary support to organizations to enable them to have systems of internal governance and self-regulation that ensure transparency and accountability and to work together towards implementation of the same;

5. In collaboration with concerned regional government bodies, establish an information center that contains data on the number of organizations operating in the country, sectors and regions in which they operate, the number of their beneficiaries and members; analyze and disseminate the same through newspapers and websites;

6. Organize regular forums for consultation between Federal and regional government bodies and civil society organizations;

7. Work in collaboration with sector administrators in carrying out its responsibilities;

8. Encourage organizations to actively participate in the development of policies and laws by the government;

9. Conduct research and advise the Government on the role of organizations in the protection of human rights, democratization and development activities of the country;

10. Develop policy guidelines to ensure that the development activities undertaken by organizations are to the extent possible aligned with the development plans issued by the government;

11. Without prejudice to the provisions of relevant laws, to exercise the powers of registration and authentication of documents with regard to Organizations;

፲፪/ የአገልግሎት ክፍያዎችን በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ መሰብሰብ፤

፲፫/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ሥም መክሰስና መከሰስ፤

፲፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለሌሎች አካላት በውክልና መስጠት፤

፲፭/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን መክፈት፤

፲፮/ በዘርፉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል የሚያስችሉ ሥራዎችን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በትብብር መሥራት፤

፲፯/ ድርጅቶች ሲፈርሱ በሒሳብ አጣሪነት የሚያገለግሉ ባለሙያዎችን ዝርዝር ማዘጋጀትና ሥራቸውን ባግባቡ ማከናወናቸውን መቆጣጠር፤

፲፰/ በዚህ አዋጅ የተቋቋመውን የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ ማስተዳደር፤

፲፱/ የበጎ ፈቃደኝነትን ባሕልና እንቅስቃሴ ማበረታታት፤የበጎ ፈቃደኝነት በተመለከተ የስርጸት ስራ መስራት፤

፳/ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚስፈልጉ ሌሎች ተግባራት ማከናወን።

**፯. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>**

ኤጀንሲው፣

ሀ/ ቦርድ ፣

ለ/ በመንግስት የሚሾም ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ እና

ሐ/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

12. Collect fees for the services it renders in accordance with the rate to be approved by the Government;

13. Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name; and,

14. Delegate, when it deems necessary, the powers and functions given to it by this Proclamation.

15. Open branch offices anywhere part of the country as it deems necessary.

16. Work in close cooperation with the relevant Government Agencies to prevent money laundering and the financing of terrorism.

17. Prepare a list of liquidators and monitor their performance in the dissolution of organizations.

18. Administer the Civil Society Fund established by this proclamation.

19. Promote a culture of volunteerism and voluntary activities and disseminating the same.

20. Undertake other activities necessary for the achievement of its objectives.

**7/ <u>Organization of the Agency</u>**

The Agency shall have:

a/ Board;

b/ A Director General and as may be necessary Deputy Director Generals to be appointed by the government; and

c/ The necessary staff.

፰. **የቦርዱ አባላት**

፩/ ቦርዱ በሚከተለው ሁኔታ የሚሰየሙ አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል።

ሀ) በጠቅላይ አቃቤ ህጉ የሚሰየሙ የሦስት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተወካዮች፣

ለ) በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የሚሰየሙ ሦስት ተወካዮች፣

ሐ) በሲቪል ማኅበረሰብ ሥራ ተገቢው ዕውቀትና ልምድ ያለውና በግል ብቃት በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የሚሾም አንድ ባለሞያ፣

መ) የሁሉም አካል ጉዳተኞች የህብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም ወይም ተሳትፎ የማሳደግና ማጠናከር ልምድና ችሎታ ያላቸውን ሁለት አባላት በራሳቸው በአካል ጉዳተኞች ማህበራት ብሄራዊ ፌደሬሽን ፣

ሠ) ከሴቶችና ወጣቶች ማህበራት በራሳቸው አደረጃጀት የሚወከሉ ሁለት አባላት ።

፪/ የቦርድ አባላት ከየትኛውም ዓይነት ተጽዕኖ ነፃ በመሆን , ሥራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ያከናውናሉ ።

፫/ የቦርዱ ሊቀመንበር በጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ የሚሾም ሲሆን የሥራ ዘመኑም ሦስት ዓመት ይሆናል።

፱/ **የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የመደራጀት መብትን አፈጻጸም በማጎልበትና በዘርፉ የሕብረተሰብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ረገድ ኤጀንሲው የሚመራባቸውን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ያስቀምጣል።

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቀርቡ ይግባኞችን ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሠጣል፣አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩን የሚመረምር ገለልተኛ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ይሰይማል፣ ኮሚቴው በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረትም አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል።

8/ **Members of the Board**

1/ The Board shall have elven members composed of:

a) Three representatives of Government bodies, designated by the Attorney General.

b) Three representatives designated by the Council of Civil Society Organizations.

c) One expert knowledgeable in the workings of civil society, to be appointed by the Attorney General on the basis of his/her competence.

d) Two members from National Federeation of Disability Associations, who have the experience and capacity to enhance and stregthen benefit and involvement of part of the society with disability.

e) Two Members reperesented from Women and Youth Associations by their own structure.

2/ The members of the Board shall undertake their responsibilities in good faith and with integrity free from any external influence.

3/ The Chairperson of the Board shall be elected by the Attorney General and his term of service shall be 3 (three) years.

9/ **Powers and Functions of the Board**

The Board shall have the following powers and functions:

1/ Set policy directions for the Agency with a view to ensuring the full exercise of freedom of association and to ensure public benefit;

2/ Hear appeals from decisions of the Director General in accordance with this Proclamation, sets up an independent complaint review committee as necessary, and give administrative decisions on the basis of the recommendations of the Committee;

፫/ የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴውን አሰራር የሚወስን መመሪያ ያወጣል አፈጻጸሙን ይከታተላል።

፬/ በዚህ አዋጅ መሠረት ድርጅቶች ሥራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ያወጣል።

፭/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርብለትን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና ሪፖርት መርምሮ ያጸድቃል።

፮/ የዋና ዳይሬክተሩና የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሥራ አፈጻጸም በየጊዜው ይገመግማል፤ የግምገማውን ውጤት መሠረት በማድረግ ዋና ዳይሬክተሩ ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አሠራሩን እንዲያሻሽል ይመክራል።

፯/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚቀርቡለትን ሌሎች ጉዳዮች መርምሮ ይወስናል።

፲/ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን

፩/ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ።

፪/ የሥራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት መልቀቅ የሚፈልግ የቦርድ አባል ጥያቄውን ለቦርዱ በጽሑፍ በማቅረብ መልቀቅ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ላይ የተመለከተው ቢኖርም በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚሰየመው የመጀመሪያው ዙር ቦርድ ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ከሚሰየሙ አባላት አንድ አባል እና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እንዲሁም በአካል ጉዳተኞች እና ሴቶችና ወጣቶች ከሚሰየም አባላት መካከል የአንድ አባል በጠቅላላው የሁለት አባላት የስራ ዘመን ለአራት አመት ይሆናል፡፡ የስራ ዘመናቸው ለአራት አመት የሆነ አባላት በድጋሚ ሊመረጡ አይችሉም ፡፡

3/ Issue Rules of procedure for the Complaint Review Committee and follow up its implementation;

4/ Issue directives to enable organizations to carry out their activities in accordance with this Proclamation;

5/ Examine and approve annual activity plans and reports submitted to it by the Director;

6/ Evaluates the performance of the Director General and Deputy Director Generals on a regular basis, and, based on the results, advises the Deputy Director to improve his performance; and,

7/ Decides on other matters submitted to it by the Director General.

**10/ Term of Office of the Board Members**

1/ The term of office of the Board members shall be 3 (three) years. Members may be re-elected for one additional term of office.

2/ A member of the Board wishing to resign before the end of his term of office may do so by submitting a notice in writing to the Board;

3/ Notwithstanding sub-article 1 of this article, from among the members of the first round Board to be appointed as per this Proclamation, one member appointed from governmental bodies and one person appointed from sivil societies organization as well as one member appointed from disables and women and youths in general two members shall have membership term of 4 years. Board members who have membership term of four years can not be Re-elected.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሰረት በተመለከተው አግባብ የሚሾሙ የስራ ዘመናቸው አራት አመት የሚሆኑ የቦርድ አባላት መጀመሪያ በጠቅላይ ዐቃቤ ህጉ ለሹመት በሚቀርቡበት ጊዜ ይለያሉ፡፡

## ፲፩. የቦርዱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

፩/ የቦርዱ ሊቀመንበር የቦርዱን ስብሰባ ይመራል። ሊቀመንበሩ በማይገኝበት ጊዜ በስብሰባው የተገኙ አባላት ከመካከላቸው ሰብሳቢውን ይሰይማሉ።

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖረው በቦርዱ ስብስባ ላይ ይሳተፋል።

፫/ የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በየሁለት ወሩ የሚካሄድ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ የቦርዱ ሊቀመንበር ወይም ከቦርድ አባላት አንድ ሶስተኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊያደርግ ይችላል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፪. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ሆኖ፣ ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ( ፩ ) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ዳይሬክተሩ፡ -

ሀ/ በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ የኤጀንሲውን ዓመታዊ ሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤

ሐ/ በተፈቀደው የኤጀንሲው የሥራና በጀት ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

4/ The board members to be appointed as per sub-article 3 of this article who will serve for term of office of 4 years shall be identified at the time of their appointment by Attorney General.

## 11/ Meeting Procedures of the Board

1/ The meetings of the Board shall be chaired by the Chairperson or, in his absence, a person designated by members in attendance from among themselves;

2/ The Director General of the Agency shall participate in meetings of the Board as a non-voting member.

3/ The regular meeting of the Board shall take place once every month. It may, however, conduct extraordinary meetings where the Chairperson of the Board or 1/3 (one third) of the members so request.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may prescribe its own rules of procedure of the meeting.

## 12/ Powers and Functions of the Director General

1/ The Director General shall be accountable to the Attorney General. He shall direct and manage the activities of the Agency in accordance with the general directions given to him by the Board.

2/ Without prejudice to the generalities of sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a. Exercise the powers and functions of the Agency specified under this proclamation;

b. Prepare the annual work plan and budget of the Agency;

c. Effect expenditures in accordance with the approved work plan and budget of the Agency;

መ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ማናቸውም ግንኙነት ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ሠ/ የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

ረ/ የኤጀንሲውን ሠራተኞች የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ ዓላማዎች ተከትሎ በመንግሥት በልዩ ሁኔታ በሚጸድቅ ደንብ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን ለምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንዲሁም ለሌሎች የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ፲፫/ የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር ሆኖ፦

፩/ የኤጀንሲውን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳል፤

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዳይሬክተሩ የተሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፤

፫/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ፲፬/ በጀት

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## ፲፭. የሒሳብ መዛግብት

፩/ ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኤጀንሲው የሒሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም በዋናው ኦዲተር በሚሰየም ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

d. Represent the Agency in all dealings with third parties;

e. Prepare the activity and financial reports of the Agency.

f. Hire and administer employees of the Agency in accordance with a special regulation to be issued by the Government in line with basic principles of federal civil service laws;

3/ The Director may delegate his powers and functions to the Deputy Director as well as to officials and employees of the Agency to the extent necessary for the efficient execution of the activities of the Agency.

## 13/ Powers and Functions of the Deputy Director General

The Deputy Director Generals shall be accountable to the Director General and, he shall:

1/ Assist the Director General in the planning, organizing, directing and facilitation of the Agency’s activities,

2/ Perform the activities of the Director in his absence;

3/ Performs the activities assigned by the Director General.

## 14/ Budget

The budget of the Agency shall be allocated by the Government.

## 15/ Books of Account

1/ The Agency shall keep complete and accurate books of account.

2/ The Agency’s books of account and any other financial documents shall be inspected every year by the Auditor General or by an Auditor who is assigned by the Auditor General.

## ክፍል ሦስት

## የድርጅቶች አመሠራረትና ምዝገባ

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፲፮/ መርሆዎች**

የድርጅቶች አመሠራረት በሚከተሉት መርሆች ይመራል:-

፩/ ማንኛውም ድርጅት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል፤

፪/ በድርጅቶች ውስጥ አባልነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው። አንድ አባል በፈለገ ጊዜ ከድርጅቱ መውጣት ይችላል፤

፫/ ማንኛውም ድርጅት አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት በማድረግ የአባላት መቀበያ መሥፈርቶችን የመወሰን መብት አለው፤

፬/ ማንኛውም ሰው የድርጅቱን መስፈርት እስካሟላ ድረስ አባል የመሆን መብት አለው፤

፭/ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምፅ አለው፤

፮/ ድርጅቶች ለአባላት ትርፍ ለማከፋፈል በማሰብ ሊቋቋሙ አይችሉም፤

፯/ የድርጅቶች አመሠራረትና የውስጥ አሰራር ዲሞክራሲያዊ መርሖችን የተከተለ፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ነፃና ገለልተኛ ሊሆን ይገባል፤

፰/ ማንኛውም ድርጅት የሚመራው በመተዳደሪያ ደንቡ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ነው፤

፱/ ማንኛውም ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ካልሆነ በቀር አባላትን ሊቀበልና ሊያሰናብት አይችልም።

፲/ ኤጀንሲው ድርጅቶች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ ሞዴል መተዳደሪያ ደንቦችን ያዘጋጃል።

## SECTION THREE

## FORMATION AND REGISTRATION OF ORGANIZATIONS

### SUB SECTION ONE

### GENERAL PROVISIONS

**16/ Principles**

The formation of organizations shall be governed by the following principles:

1/ An organization may be formed for definite or an indefinite period;

2/ Membership in any organization shall be voluntary. A member may withdraw from membership at will.

3/ An organization shall have the right to freely determine the criteria for membership;

4/ Any person has the right to become a member in as long as he fulfills the criteria for membership set by the organization;

5/ Every member shall have equal vote.

6/ Organizations may not be established for the purpose of distributing profit to members;

7/ The formation and internal governance of organizations shall be based on democratic principles, non-discriminatory, independent and neutral.

8/ An organization shall be managed by persons elected by the full participation of the organs authorized by its rules ;

9/ An organization may not admit or dismiss members except in accordance with its rules.

10/ The Agency shall prepare model rules that may be used by Organizations.

**፲፯/ የአገር በቀል ድርጅቶች አመሰራረት**

ቁጥራቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች አገር በቀል ድርጅት ሊመሰርቱ ይችላሉ።

**፲፰/ የአገር በቀል ድርጅት ዓይነቶች**

ለዚህ ክፍል ዓላማ የአገር በቀል ድርጅት በሚከተለው አይነት አደረጃጀ ሊቋቋም ይችላል።

፩/ ማኅበር፣

፪/ ቦርድ-መር ድርጅት፣

፫/ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት፣

፬/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት፣

፭/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴ።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ማህበርና ቦርድ-መር ድርጅት

**፲፱/ ማኅበር**

፩/ ለዚህ ክፍል አላማ ማኅበር ማለት፣ ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት የሚቋቋም እና ጠቅላላ ጉባዔው የበላይ ውሳኔ ሰጪ አካል የሆነበት ድርጅት ሲሆን፣ ለዚህ ሕግ አፈጻጸም የሙያ ማኅበራትን ይጨምራል።

፪/ አንድ ማኅበር፣ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የሥራ ክፍሎች ያለው ሆኖ ሊደራጅ ይችላል። የማኅበሩ አወቃቀርና አስተዳደር በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል።

**፳. ቦርድ-መር ድርጅት**

፩/ ለዚህ ክፍል አላማ ቦርድ-መር ድርጅት፣ ቁጥራቸው ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሥራቾች የሚቋቋም ሲሆን፣ የድርጅቱ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ቦርዱ ይሆናል።

፪/ ቦርዱ ቁጥራቸው ከ፭ እስከ ፲፫ የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።

**17/ Formation of Local Organizations**

Two or more persons may establish an indigenous organization.

**18/ Types of Local Organizations**

For the purpose of this Sub-section local organization may be formed as:

1/ An association;

2/ A Board-led Organization;

3/ A charitable endowment;

4/ A charitable trust; or

5/ A Charitable Committee.

## SUB SECTION TWO
## ASSOCIATIONS AND BOARD LED ORGANIZATIONS

**19/ Association**

1/ For the purpose of this Sub-section An association is an organization formed by five or more members and governed by a General Assembly as the supreme decision-making body; for the purpose of this Proclamation it shall include professional associations.

2/ An association may have a General Assembly, Executive Committee, Manager, Auditor and other departments as may be necessary. Details regarding the structure and governance of an association will be determined by its rules.

**20/ Board-led Organization**

1/ For the purpose of this sub-section board-led organization means formed by two or more founders, its Board being the supreme organ.

2/ The board shall have a minimum of five and a maximum of thirteen members.

፫/ የመጀመሪያዎቹ የቦርዱ አባላት በመመስረቻ ጽሑፉ ላይ በመሥራቾቹ ይሰየማሉ። የቦርድ አባላት የሥራ ዘመንና ከምስረታ በኋላ የቦርድ አባላት የሚሰየሙበት ስርዓት በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

፬/ ከድርጅቱ የሥራ መሪዎች ጋር የስጋ እና የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሰዎች የቦርድ አባል መሆን አይችሉም።

፭/ ድርጅቱ ለቦርዱ ተጠሪ የሆነ ሥራ አስኪያጅ እና አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል። ዝርዝሩ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## የዘለቄታ የበጎ አድራጎት ድርጅት

### ፳፩/ መሠረቱ

፩/ ለዚህ ክፍል አላማ "የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት አንድ የተለየ ንብረት፣ገንዘብ በስጦታ ወይም በኑዛዜ በዘላቂነትና በማይመለስ ሁኔታ ተለይቶ ለተገለጸ የበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ የሚውልበት ድርጅት ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሰረት በስጦታ ወይም በኑዛዜ የሚሰጠው የንብረት ወይም የገንዘብ መጠን የበጎ አድራጎት አላማውን በመነሻነት ለማሳካት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

፫/ መሥራቹ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ተጠቃሚዎች ይወስናል። መሥራቹ ተጠቃሚዎቹን በበቂ ሁኔታ ካልወሰነ የሥራ አመራር ቦርዱ ከመሥራቹ ሀሳብ ጋር ይስማማል ብሎ በሚገምተው መልኩ ተጠቃሚዎችን ሊወስን ይችላል።

3/ The first board members shall be designated by the founders. The term of service and appointment procedures for subsequent board members shall be prescribed by the rules of the organization.

4/ Persons who are related by consanguinity or affinity with the officers of the Organization may not be Board members.

5/ A board-led organization shall have a manager accountable to the Board and necessary staff as may be necessary. The particulars shall be determined by the rules of the organization.

## SUB SECTION THREE
## CHARITABLE ENDOWMENTS

### 21/ Basis

1/ For the purpose of this Sub-section A "Charitable Endowment" is an organization by which a certain property is perpetually and irrevocably destined by donation, money or will for a purpose that is solely charitable.

2/ Property or money provided through Gift or will based on sub articel 1 of this provision shall be sufficient to fulfill the purpose the charity initially.

3/ The founder shall determine the beneficiaries of a charitable endowment. Were the beneficiaries are not sufficiently determined by the founder, the Board may determine such beneficiaries as it deems consistent with the intentions of the founder.

.

## ፳፪/ ለምዝገባ ስለማመልከት

፩/ መሥራቹ በሕይወት ሳለ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ምዝገባ የሚጠየቀው በመሥራቹ በራሱ ወይም ለዚህ ጉዳይ በወከለው ሰው ብቻ ነው።

፪. መሥራቹ ከሞተ በኋላ ጥያቄው የሚቀርበው ከመሥራቹ አደራ በተቀበለው ሰው ወይም የመሥራቹን ኑዛዜ በሚያስፈጽሙ ሰዎች ነው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሱት በማይኖሩበት ጊዜ ለዘለቄታ ንብረትን ለበጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ውል ያዘጋጁ፣ ምስክር የሆኑ ወይም ውሉን በአደራ ያስቀመጡ ሰዎች የምዝገባ ጥያቄ ያቀርባሉ።

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ምዝገባ የመጠየቅ ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች ምዝገባውን ሳይጠይቁ የቀሩ እንደሆነ መሥራቹ ከሞተ ከሦስት ወር በኋላ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ማንኛውም ይመለከተኛል በሚል ሰው አመልካችነት ወይም በኤጀንሲው አነሳሽነት ሊመዘገብ ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፬ መሠረት የሶስት ወራት ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ለበጎ አድራጎት ድርጅት ዓላማው የሚውለውን ገንዘብ ወይም ንብረት እና አጠቃላይ የምዝገባውን አካሔድ አስመልክቶ ዓላማውን የሚጻረር ተግባር ከተፈፀመ ኤጀንሲው በማንኛውም ጊዜ ጣልቃ መግባትና ማስተካከል ይችላል።

## ፳፫/ ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባርን መሻር

ንብረትን ለዘለቄታ በጎ አድራጎት ዓላማ የመስጠት ተግባር በኤጀንሲው ከመመዝገቡ በፊት መሥራቹ ሊሽረው ይችላል።

## 22/ Application for Registration

1/ The registration of a Charitable Endowment may not be sought during the lifetime of the founder, except by the founder herself/himself or a person delegated by the founder for that purpose.

2/ After the death of the founder, it shall be sought by the person to whom the founder has entrusted such task and who has accepted it or by the executors of the founder's will.

3/ In default of the persons specified in Sub-article (1) and (2), it shall be sought by those persons who have drawn up the act of Endowment or who have been witnesses to it or who hold that act in deposit.

4/ Where the persons who are bound to seek the registration of the Charitable Endowment fail to do so, the registration of the Charitable Endowment may be sought, three months after the death of its founder , by any interested party or by the Agency.

5/ When any activity contrary to the aim of the registration or concerning the property or money and the whole registration process is occurred before the end of the three months indicated under sub article 4 of this article the Agency can intervene at any time.

## 23/ Revocation of an Act of Charitable Endowment

The founder of an endowment may revoke it so long as the Charitable Endowment has not been registered by the Agency.

**፳፬/ የዘለቂታ የበጎ አድራጎት ድርጅት አደረጃጀት**

ማናቸውም የዘለቂታ በጎ አድራጎት ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተርና ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች ይኖሩታል።

**፳፭/ የሥራ አመራር ቦርድ ጥንቅር**

፩/ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በመሥራቹ ወይም እርሱ በወከለው ሰው ይሾማሉ። የቦርድ አባላቱ በዚህ መልክ ካልተሾሙ ኤጀንሲው የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል።

፪/ አንድ የሥራ አመራር ቦርድ አባል በማንኛውም ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት ካልቻለ በዘለቂታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አዲስ የቦርድ አባል ይሾማል።

፫/ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ቁጥር ከሦስት በታች ሊሆን አይችልም።

**፳፮/ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣን እና ተግባራት**

የሥራ አመራር ቦርዱ የዘለቂታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ የበላይ አካል ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩/ ዘለቂታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን የሚመራ ሥራ አስኪያጅ እና ኦዲተር ይሾማል፤ ያሰናብታል፤

፪/ የዘለቂታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱን በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ያስተዳድራል።

**፳፯. የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባዎች**

፩/ የሥራ አመራር ቦርዱ በዘለቂታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በተመለከተው መሠረት ይሰበሰባል።

፪/ የዘለቂታ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የሥራ አመራር ቦርድ ውሳኔዎችን የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ይሆናል።

**24/ Structure of Charitable Endowments**

Any Charitable Endowment shall be organized with the structure of Management Board, Manager, Auditor and other departments as may be necessary.

**25/ Composition of the Management Board**

1/ Members of the Management Board shall be appointed by the founder or by a person delegated by the founder. Where the founder or his delegated has not appointed members of the Management Board, the Agency shall facilitate the appointment of such members.

2/ Where a member of management the Board is for any reason unable to perform his duties, a new member shall be appointed according to the rules of the Endowment.

3/ The number of members of the Management Board shall in no case be less than three.

**26/ Powers and Functions of the Management Board**

The Management Board shall be the supreme organ of the Chairtable Endowment and shall have the following powers and functions:

1/ Appoint a Manager who shall be responsible to manage the Endowment or dismiss the same; and

2/ Administer the Endowment in accordance with its rules.

**27/ Meetings of the Management Board**

1/ The Management Board shall meet as prescribed by the rules of the Charitable Endowment.

2/ The decisions of the Management Board shall be taken by majority.

**፳፰/ ለቦርዱ አባላት የሚፈፀሙ ክፍያዎች**

፩/ በዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ካልተወሰነ በስተቀር አንድ የቦርድ አባል ክፍያ አያገኝም።

፪/ በቦርድ ስብሰባ ላይ ለመገኘት አንድ አባል ያወጣውን ወጪ ለመሸፈን የሚደረግ ማካካሻ እንደ ክፍያ አይቆጠርም።

**፳፱/ የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን እና ተግባራት**

የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፡-

፩/ የዘለቄታ በጎ አድራጎት የድርጅቱን ሥራ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ይመራል፤

፪/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፤

፫/ የሥራ አመራር ቦርዱ ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤

፬/ የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ እና የሒሳብ ሪፖርቶችን ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፤

፭/ የድርጅቱን ገቢ የሚያሳድጉ ሁኔታዎችን ያጠናል፣ በሥራ አመራር ቦርዱ ሲፀድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮/ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በድርጅቱ ሥም የተከፈቱ የባንክ ሂሳቦችን ያንቀሳቅሳል፤

፯/ ሌሎች በሥራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ተያያዥ ተግባራት ያከናውናል።

**፴. የኦዲተር ሥልጣን እና ተግባራት**

ኦዲተሩ፡-

፩/ የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ይቆጣጠራል፣

፪/ የድርጅቱን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ የሒሳብ አያያዝ መርሆች መሠረት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።

**28/ Remuneration of Board Members**

1/ A Member of the Board shall not be entitled to remuneration unless a provision about his entitlement to remuneration has been made, by the Charitable Endowment's rules or by any law.

2/ Payments made in connection with covering costs incurred by Board Members for the purpose of attending Board meeting shall not be considered as remuneration.

**29/ Powers and Functions of the Manager**

The manager of the Charitable Endowment shall:

1/ Direct the work of the Charitable Endowment pursuant to its rules;

2/ Represent the Endowment in all its dealings with the third parties;

3/ Follow up and supervise the implementation of the decisions of the Management Board;

4/ Submit work plan and budget as well as activity and financial reports to the Management Board;

5/ Study conditions that will promote income generation for the Endowment and implement such where approved by the management Board;

6/ Operate bank accounts opened in the name of the Endowment in accordance with its rules; and

7/ Discharge other related tasks which may be given to him by the Management Board.

**30/ Powers and Functions of the Auditor**

The Auditor shall:

1/ Monitor the financial and proprietary administration of the Charitable Endowment;

2/ Prepare the internal audit report of the organization in accordance with accounting standards acceptable in Ethiopia;

## ንዑስ ክፍል አራት
## የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት

**፴፩/ መሰረቱ**

ለዚህ ክፍል አላማ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ማለት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በሚያቋቁመው ሠነድ መሠረት አንድ የተለየ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ብቻ እንዲውል በባለአደራዎች የሚተዳደር ድርጅት ነው።

**፴፪/ አመሰራረት**

፩/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ፣ በኑዛዜ ወይም አግባብ ባለው የመንግስት አካል ውሳኔ ሊቋቋም ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ስጦታ ወይም ኑዛዜ አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይመራል።

፫/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት መሥራች የሆነ ሰው ማቋቋሚያ ሰነድ፤ መሥራቹን፣ ባለአደራዎቹንና የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ተጠቃሚዎች በግልጽ ለይቶ ማስቀመጥ አለበት።

**፴፫/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ቀጣይነት**

፩/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ሊቋቋም ይችላል።

፪/ ላልተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ዘላቂና የማይሻር ይሆናል።

**፴፬. በባለአደራዎች የሚቀርብ የምዝገባ ማመልከቻ**

፩/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት መሥራች የሆነ ሰው ባለአደራዎቹን መሾም አለበት።

፪/ ባለአደራዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ በተደነገገው መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ለኤጀንሲው የምዝገባ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።



## SUB SECTION FOUR
## CHARITABLE TRUST

**31/ Basis**

For the purpose of this Sub-section "Charitable Trust" is an organization established by an instrument by which specific property is constituted solely for a charitable purpose to be administered by persons, the trustees, in accordance with the instructions given by the instrument constituting the charitable trust.

**32/ Formation**

1/ A Charitable Trust may be established by a donation or by a will or by the decision of the concerned government body.

2/ A donation or will under Sub-article (1) of this Article shall be governed by the relevant provisions of civil code.

3/ A document which established a charitable trust shall clearly specify the founder, the trustees and beneficiaries of the charitable trust.

**33/ Perpetuity of a Charitable Trust**

1/ A Charitable Trust may be established for a definite or an indefinite period.

2/ Where a Charitable Trust is established for an Indefinite period, it shall be perpetual and irrevocable.

**34/ Application for Registration by Trustees**

1/ The founder of a charitable trust shall appoint trustees.

2/ The Trustees shall apply to the Agency for a certificate of registration in the manner provided in Article 57 of this Proclamation.

፫/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት የምዝገባ ጥያቄ ድርጅቱ በተመሠረተ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርበታል።

፬/ ባለአደራዎቹ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከማግኘታቸው በፊት በስጦታው ወይም በኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ሀብት ባለይዞታነት ወይም ባለቤትነት ወደ አደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለማስተላለፍ ከሚያስፈልጉ ድርጊቶች በስተቀር በሀብቱ ላይ ሦስተኛ ወገኖችን የሚያካትት ማናቸውንም ድርጊት መፈፀም አይችሉም።

## ፴፭. የባለአደራዎች ብዛት

፩/ የባለአደራዎች ብዛት ከሦስት ያነሰ እና ከአምስት የበለጠ ሊሆን አይችልም። ከሦስት ያነሱ ሰዎች ተሾመው ከሆነ ይህን መመዘኛ ለማሟላት ኤጀንሲው ቀሪዎቹ ባለአደራዎች የሚሾሙበትን መንገድ ያመቻቻል።

፪/ ከአምስት በላይ ባለአደራዎች ተሾመው ከሆነ በቅድሚያ የተጠቀሱት መሥራት የሚችሉና ፈቃደኝነት ያላቸው አምስት ሰዎች ብቻ ባለአደራ ይሆናሉ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ወይም ከዚያ በላይ ድርጅቶች በባለአደራነት ተሾመው ከሆነ የባለአደራዎቹ ብዛት ከሦስት በታች እንዲሆን ኤጀንሲው ሊፈቅድ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከሚሾሙት ባለአደራዎች ቢያንስ አንዱ መደበኛ መኖሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ መሆን አለበት።

## ፴፮/ የባለአደራዎች አሿሿም

፩/ ባለአደራ የሚሾመው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያቋቋመው ሰው ወይም እርሱ የወከለው ሰው ነው። እነዚህ ሰዎች ከሌሉ ኤጀንሲው ባለአደራ የሚሾምበትን መንገድ ያመቻቻል።

፪/ የተሾመው ባለአደራ ይህን ኃላፊነት አልቀበልም ካለ ወይም በማናቸውም ምክንያት ባለአደራነቱን ማከናወን ካልቻለ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ሌላ ባለአደራ ይሾማል።

3/ An application for the registration of a Charitable Trust shall be submitted within 3 months from the formation of the Charitable Trust.

4/ The trustees may not perform any acts involving third parties before acquiring a certificate of registration except those acts necessary for transferring the resource mentioned in the donation or will to the possession or ownership of the Charitable Trust.

## 35. Number of Trustees

1/ The number of trustees shall not in any case be lower than three and more than five. Where less than three persons are appointed, the Agency shall facilitate the appointment of the number of people required to fulfill this requirement.

2/ Where more than five persons are appointed, as trustees, the five first named persons who are able and willing to act shall alone be the trustees.

3/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Agency may allow less than 3 persons as trustees where one or more of such trustee is a Charity.

4/ At least one of the trustees appointed under this Article shall be an Ethiopian domiciliary.

## 36/ Appointment of Trustees

1/ The trustees may be appointed by the person who founded the Trust or by the person designated by him. In the absence of such appointment the Agency shall facilitate the appointment of trustees.

2/ Where the trustee so appointed refuses his agency or is for any other reason unable to perform the trusteeship, a new trustee shall be appointed according the rules of the trust.

## ፴፯/ ድርጅትን በባለአደራነት መሾም

፩/መሥራቹ ሕጋዊ ሰውነት ያለውን ድርጅት በባለአደራነት ከሾመ፣ የተሾመው ድርጅት ሥራ መሪዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ያስተዳድራሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው ድርጅት የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በኑዛዜው፣ በስጦታው ወይም በኤጀንሲው ትዕዛዝ በተወሰነው መሠረት ከሌሎች ስጦታዎች ወይም ዓላማውን ለማሳካት ከሚጠቀምበት ገቢ ለይቶ በመያዝ ያስተዳድራል።

## ፴፰. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አደረጃጀት

፩/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን ሥራ አስኪያጅ፣ ገንዘብ ያዥ እና ኦዲተር በመሥራቹ ወይም መሥራቹ በወከለው ሰው ይሾማሉ።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከቱትን ኃላፊዎች መሥራቹ ወይም በመሥራቹ የተወከለው ሰው ያልሾመ እንደሆነ ባለአደራዎቹ ከመካከላቸው ወይም ከውጭ ኃላፊዎቹን ይሰይማሉ።

፫/ ባለአደራዎቹ በንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ኃላፊዎቹን ያልሰየሙ እንደሆነ ኃላፊዎቹ በኤጀንሲው ይሾማሉ።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ባለአደራዎች ኃላፊነታቸውን በጋራ ያከናውናሉ።

፭/ ባለአደራዎቹ ስብሰባቸውን የሚመራ ሊቀመንበር ከመካከላቸው ይመርጣሉ።

## 37/ Appointment of a Charity as a Trustee

1/ If the founder has appointed an organization which has a legal personality as a trustee, the officers of the appointed organization will administer the trust.

2/ The Charity provided in Sub-article (1) shall administer the charitable trust by the terms of the will, donation or order of the Agency and distinguish it from other donations or income that it utilizes to achieve its purposes.

## 38/ Structure of a Charitable Trust

1/ The manager, treasurer and auditor of a charitable trust shall be appointed by the founder, or delegated by the founder.

2/ If these officers are not appointed by the founder, delegated by his delegatee, the trustees shall designate the same from among themselves or third parties.

3/ The Agency shall make such designation where the trustees fail to make such designation or are unable to give decision.

4/ Notwithstanding sub Article (1) of this provision, trustees shall execute their responsibilities jointly.

5/ The trustees shall among themselves choose the person who shall serve as the chairperson in the meetings of the trustees.

## ፴፱/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት አስተዳደር

፩/ ከባለአደራዎች በጽሑፍ ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ሥራ አስኪያጁ የሌሎች ባለአደራዎች ስምምነት ሳያስፈልገው የማስተዳደር ሥራዎችን ይፈጽማል።

፪/ ከማስተዳደር ሥራዎች ውጭ ያሉና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተቃውሞ የቀረበባቸው ውሳኔዎች ከባለአደራዎች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱ በተገኙበት ስብሰባ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል።

፫/ ከባለአደራዎች ውስጥ እኩል ድጋፍ ያላቸው የተለያዩ ሃሣቦች ሲቀርቡ የመጨረሻው ውሣኔ የስብሰባው ሊቀመንበር በሚሰጠው ድምፅ ይወሰናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት በተሰጡ ውሳኔዎች የማይስማሙ ባለአደራዎች የልዩነት ሃሣባቸው በቃለ ጉባኤው ላይ እንዲመዘገብላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

## ፵. የባለአደራዎቹ ኃላፊነት

፩/ ባለአደራዎች ከአንድ መልካም የቤተሰብ አስተዳዳሪ በሚጠበቀው ትጋትና ጥንቃቄ ድርጅቱን ማስተዳደር አለባቸው።

፪/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ባለአደራዎቹ ከኤጀንሲው ፈቃድ ውጭ የድርጅቱን ንብረት ለሌላ ሰው ሊያስተላልፉ አይችሉም።

፫/ ባለአደራዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ያለ ዋጋ ለሌላ ሊያስተላልፉ አይችሉም።

፬/ ባለአደራዎቹ በአደራ በጎ አድራጎት ሥራ መሪነታቸው ከሥልጣናቸው በላይ በፈጸሙት ተግባር ወይም በሰጡት ውሳኔ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ። ሆኖም በአንቀጽ ፴፱(፬) መሠረት ከውሳኔው መለየቱን ያስመዘገበ ባለአደራ በውሳኔው ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።

## 39/ Administration of a Charitable Trust

1/ The manager shall perform all acts of management without the approval of the other trustees except where at least one of the trustees submits a written protest concerning any administrative act.

2/ Decisions beyond acts of management and those decisions protested to under Sub-article (1) shall be taken by majority where at least three of the trustees are present.

3/ Where opposing notions are supported by an equal number of trustees, the final determination shall lie with the vote of chairperson of the meeting.

4/ Those who are against a decision taken under Sub-article (2) and (3) may require that their dissenting opinion be recorded in the minutes.

## 40/ Obligation of Trustees

1/ Trustees shall administer the Trust with due diligence and care expected from a responsible family head.

2/ Without prejudice to any provision to the contrary in the act of constitution of the Charitable Trust, the trustees may not alienate immovable property without prior notification to the Agency.

3/ The trustees may not alienate the property of a Charitable Trust by a gratuitous title.

4/ The trustees shall be jointly and severally liable for any damage caused to the trust due to the ultra vires acts or decisions they take as officers of the charitable trust. However, a trustee who has registered his dissent from the decision of the trustees in accordance with Article 39(4) shall not be held liable.

**፵፩. የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅትን ስለመወከል**

፩/ ሥራ አስኪያጁ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ይወክላል።

፪/ ሥራ አስኪያጁ በርሱ ምትክ ድርጅቱን የሚወክለውን ባለአደራ ይመርጣል፣ ማናቸውም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ጉዳዮች የሚከታተል ጠበቃ ሊወክል ይችላል።

፫/ ባለአደራዎቹ ከሥልጣን ወሰናቸው ሣያልፉ ለፈፀሟቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ተጠያቂ የሚሆነው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ነው።

**፵፪. የማቋቋሚያ ሰነዱ ትዕዛዞች**

፩/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ካቋቋመው ሰነድ የተቀበላቸውን ግልጽ የሆኑ ትዕዛዞች ባለአደራው መከተል አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ተጠቃሚ ለሆነው ሰው ጥቅም የሚያስፈልግ ሆኖ የታየ እንደሆነ ከተባሉት ትዕዛዞች ውጭ ለመሥራት ባለአደራው ከኤጀንሲው ፈቃድ መጠየቅ ይችላል።

**፵፫/ ለባለአደራዎች የሚፈፀም ክፍያ**

፩/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ በተቋቋመበት ሠነድ ወይም በማናቸውም ሌላ ሕግ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር አንድ ባለአደራ ክፍያ የማግኘት መብት አይኖረውም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም አንድ ባለአደራ ለአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ለሰጠው ወይም የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን በመወከል ለፈጸመው ሙያዊ አገልግሎት ክፍያ ሊፈጸም እንደሚገባ ሁሉም ባለአደራዎች በጽሁፍ ሲስማሙ እና ኤጀንሲው ሲያፀድቅ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ሀብት ተመጣጣኝ ክፍያ ያገኛል፣

**41/ Representation of a Charitable Trust**

1/ The trustee manager shall represent the Charitable Trust.

2/ The trustee manager shall designate the trustee who shall act in his stead and may also appoint an advocate to represent the Charitable Trust in any proceedings.

3/ The Charitable Trust shall be liable for acts of trustees within the scope of their authority.

**42/ Order of Establishment Document**

1/ A trustee shall adhere to the orders under the establishment document of the trust.

2/ Notwithstanding the stipulations under sub article 1 the trustee may ask for permission from the Agency to operate beyond the orders on the establishment document when it is essential to do so for the interest of its beneficiaries.

**43/ Remuneration of Trustees**

1/ A trustee shall not be entitled to remuneration unless this is specifically stated in establishment document the trust instrument or by any law.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, a trustee who acts in a professional capacity shall be entitled to receive reasonable remuneration out of the trust funds for any services that he provides to or on behalf of the trust if all the trustees have agreed in writing and it is approved by the Agency that he may be remunerated for the services.

፫/ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ አንድ ባለአደራ በግሉ ያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

3/ A trustee is entitled to indemnity for all personal expenses and obligations arising out of the administration of the Charitable Trust.

## ፵፬/ የባለአደራው ሥራ መልቀቅ

፩/ ባለአደራው ሥራ የመልቀቅ ሀሳብ ካለው ሥራውን ከመልቀቁ ከሁለት ወር በፊት ለሌሎች ባለአደራዎች ሊያሳውቅ ይገባል፡፡ይህን ሳያስታውቅ ቢቀር ከዚህ የተነሣ በአደራ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ኪሣራ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪/ ባለአደራው ሥልጣኑን ለሌላ ባለአደራ እስከሚያስተላልፍ ድረስ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፡፡

፫/ አንድ ባለአደራ የሥራ መልቀቂያ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከማለፉ አንድ ወር አስቀድሞ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ባቋቋመው ሰው ወይም ይህን ለመፈጸም ሥልጣን በተሰጠው ሰው፣ ወይም እነዚህ ባይኖሩ በኤጀንሲው አዲስ ባለአደራ ይሾማል፡፡

## 44/ Resignation of a Trustee

1/ A trustee shall be liable for any consequent loss to the Charitable Trust where he does not notify the other trustees and the Agency of his intention to resign two months prior to his resignation.

2/ A trustee shall remain responsible for the administration of the charitable trust until he hands over the trusteeship.

3/ Where a trustee applies for resignation, a new trustee shall be appointed by the person constituting the trust, by the person on whom such power has been conferred, or in default of any Such person, by the Agency 1 month prior to the expiry of the notice prescribed in sub-article (1).

## ፵፭ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ማስያዝ

፩/ የተጠቃሚዎች ባለገንዘቦች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ወይም ተጠቃሚው ሊያገኝ የሚገባውን አበል በማናቸውም ሁኔታ ማስያዝ አይችሉም፡፡

፪/ ለተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅት ሲፈርስ ንብረቱን የመውሰድ መብት ያላቸው ባለገንዘቦች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ንብረት ማስያዝ ይችላሉ፡፡

## 45/ Attaching Charitable Trusts

1/ The creditors of beneficiaries may in no case attach a Charitable Trust or any allowance to which a beneficiary is entitled.

2/ The creditors of persons who are to receive the property forming the object of the Charitable Trust constituted for a definite period may at the dissolution of the Charitable Trust attach such property.

**፵፮/ በሽያጭ ስለማስተላለፍ**

ማንኛውም በጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ንብረቱን ለሌላ ሶስተኛ ወገን በሽያጭ ሲያስተላልፍ ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከቀረጥ ነጻ የገባ ንብረት ከሆነ ሽያጩ በሀገሪቱ የጉምሩክ ህግ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፵፯/ የተጠቃሚዎች መብት**

፩/ ተጠቃሚዎች በአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ሠነድ መሠረት የሚገባቸው ጥቅም እንዲሰጣቸው የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱን ሊጠይቁ ይችላሉ።

፪/ ተጠቃሚዎች መብቶቻቸውን የሚጎዳ ሁኔታ ሲፈጠር ባለአደራው እንዲሻር ወይም ተገቢ የሆነ ዋስትና እንዲሰጥ ኤጀንሲውን መጠየቅ ይችላሉ።

፫/ ተጠቃሚዎች የአደራ በጎ አድራጎት ድርጅቱ አካል በሆኑ ንብረቶች ላይ በግልም ሆነ በጋራ የማዘዝ ወይም የማስተዳደር መብት የላቸውም።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ የተደነገገው ቢኖርም እነዚህን ንብረቶች በሚመለከት የይርጋ ዘመን እንዲቋረጥ ማድረግን በመሳሰለው ሥራ መብቶቻቸውን የመጠበቅ ሥራዎችን ብቻ መፈፀም ይችላሉ።

**ንዑስ ክፍል አምስት**

**ስለበጎ አድራጎት ኮሚቴ**

**፵፰/ መሰረቱ**

ለዚህ ክፍል አላማ የበጎ አድራጎት ኮሚቴ ማለት ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ለበጎ አድራጎት ዓላማ ከሕዝብ ለመሰብሰብ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው።

**46/ Transfer on Sale**

Any Charitable Organization or association while transferring its property to third party on sale, if the property is imported with out being accustom for the sake of public interest the sale shall be done in accordance with the custom law of the country.

**47/ Rights of Beneficiaries**

1/ The beneficiaries may claim from the Charitable Trust the making over of the interest, which, according to the act of constitution of the Charitable Trust, is to accrue in their favor.

2/ When the rights of beneficiaries are jeopardized, they may apply to the Agency for the dismissal of the trustee or to compel him to give appropriate guarantees.

3/ The beneficiaries of the Charitable Trust have no right to dispose of or to administer the property forming the object of the Charitable Trust jointly or severally.

4/ Notwithstanding the provision of Sub Article (3) of this Article, beneficiaries of a Charitable Trust may only carry out those acts which their rights, such as the interruption of a prescription in relation to such property.

**SUB SECTION FIVE**

**CHARITABLE COMMITTEES**

**48/ Basis**

A “Charitable committee” is a collection of five or more persons who have come together with the intent of soliciting money or other property from the public for purposes that are charitable.

**፵፱/ <u>የበጎ አድራጎት ኮሚቴን ስለማፅደቅ</u>**

፩/የበጎ አድራጎት ኮሚቴ በኤጀንሲው ሳይፀድቅ ገንዘብም ሆነ ንብረት ማሰባሰብ ወይም ማናቸውም ድርጊት መፈፀም አይችልም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ኮሚቴውን ለማቋቋም በሚደረጉ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

፫/ ኤጀንሲው የበጎ አድራጎት ኮሚቴዎችን ሲያፀድቅ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፶፱ እና ፷፪ ድንጋጌዎች በማገናዘብ መወሰን አለበት።

**፶/ <u>የሒሳብ መግለጫ</u>**

፩/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት።

፪/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተቋቋመው ከአንድ ዓመት ላነሰ ጊዜ ከሆነ ይህ ጊዜ እንዳለቀ የሒሳብ መግለጫ ማቅረብ አለበት።

**፶፩/ <u>የበጎ አድራጎት ኮሚቴ አደረጃጀት</u>**

፩/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴን የሚያቋቁም ውሳኔ መሥራች አባላቱን፣ የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ፕሬዚዳንት፣ ገንዘብ ያዥና ኦዲተር ዝርዝር ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል።

፪ ውሳኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴውን ዓላማዎች እና ዓላማዎቹን የሚያሳካበትን ጊዜ መግለፅ ይኖርበታል።

፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ውሳኔው የበጎ አድራጎት ኮሚቴው ሥራዎች እንዴት መከናወን እንዳለባቸው መወሰን እና በኮሚቴው የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና ንብረት መጠንና አጠቃቀሙን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ማስቀመጥ ይኖርበታል።ዝርዝሩ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።



**49/ <u>Approval of Charitable Committees</u>**

1/ Charities Committees shall not collect funds or perform any other activities without acquiring an approval from the Agency.

2/ Sub-article (1) of this Article shall not apply to activities necessary for the formation of a charitable committee.

3/ The Agency shall consider Articles 59 and 62 of this Proclamation when approving a charitable committee.

**50/ <u>Statement of Accounts</u>**

1/ A Charitable committee shall submit its annual statement of accounts to the Agency.

2/ A Charitable committee should submit its statement of accounts at its dissolution where the period for which the charitable committee is formed is less than one year.

**51/ <u>Structure of a Charitable committee</u>**

1/ The decision establishing the charitable committee shall specify the particulars of persons who found the charitable committee and those who shall act as president, treasurer and auditor of the Charitable committee.

2/ The decision shall specify the purposes of the Charitable Committee and the time within which it has to achieve them.

3/ The decision shall determine, where appropriate, the manner in which the activities of the Charitable committee may be carried out and prescribe such measures that are necessary to control the amount and the use of the funds and property collected by the Charitable committee. Particulars shall be determined by Directives issued by the Agency.

**፶፪/ የአባላት ኃላፊነት**

፩/ ከበጎ አድራጎት ኮሚቴው እንቅስቃሴ ለሚመነጩ ግዴታዎችና ዕዳዎች አባላት በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ ይሆናሉ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገውን በተመለከተ ኤጀንሲው፣የዘርፍ አስተዳዳሪው፣ ማናቸውም ለጋሽ፣ አባል ወይም ተጠቃሚ፣ በኮሚቴው አባላት ላይ ክስ የማቅረብ መብት አላቸው።

**፶፫/ በቂ ያልሆነ ገንዘብና ንብረት**

፩/ በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት የኮሚቴውን ዓላማ ለማሳካት በቂ ካልሆነ ወይም ዓላማውን ማሳካት የማይቻል ከሆነ ይህ ገንዘብ ወይም ንብረት የኮሚቴው መቋቋም በፀደቀበት ውሳኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በሥራ ላይ ይውላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በፀደቀው ውሳኔ ውስጥ የተመለከተ ነገር ከሌለ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ለስጦታ አድራጊዎቹ ተመላሽ ይሆናል።

፫/ ለበጎ አድራጎት ኮሚቴው ገንዘብ ወይም ንብረት የሰጡ ሰዎች መልሰው ሊወስዱት ካልፈለጉ ወይም ካልቻሉ ወይም የማይታወቁ ከሆነ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በኤጀንሲው ውሳኔ ለተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ይውላል።

**፶፬/ ቀሪ ገንዘብና ንብረት**

፩/ በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው በላይ ከሆነ ቀሪው ገንዘብ ወይም ንብረት ኮሚቴው ባፀደቀው ውሳኔ መሠረት ለሌላ ተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ሥራ ላይ ይውላል።

፪/ በውሳኔው ውስጥ ይህንን በሚመለከት የተገለፀ ነገር የሌለ እንደሆነ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለሌላ ለተመሳሳይ የበጎ አድራጎት ዓላማ ይውላል።

**52/ Liability of Members**

1/ The members of a Charitable Committee shall be jointly and severally liable for obligations and debts arising out of its activities.

2/ Any donor, member, beneficiary, the Agency or the Sector Administrator shall have standing for the purpose of sub-article 1.

**53/ Insufficient Fund and Property**

1/ Where the money or property collected by the charitable committee is insufficient to attain the object which the charitable committee proposed to achieve, or where achievement of its purpose becomes impossible, such money or property shall have the destination prescribed by the decision which has approved the charitable committee.

2/ In absence of a provision, to that effect the money or property shall be returned to the persons who have donated the money or property.

3/ If Persons who have donated money or property to the Charitable committee cannot or do not want to claim it back, the money or property shall be placed at the disposal of the Agency and shall be destined for a similar charitable purpose in accordance with the provisions of this Proclamation.

**54/ Balance**

1/ Where the money or property collected by the charitable committee amounts to more than what is necessary for the attainment of the proposed purpose, the balance shall have the destination for another charitable purpose prescribed by the decision approved by the charitable committee.

2/ In the absence of any Provision to that effect, it shall be placed at the disposal of the Agency and shall be destined for a similar charitable purpose in accordance with the provisions of this Proclamation.

**፶፭/ ወደ ዘላቂ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ስለመለወጥ**

፩/ የበጎ አድራጎት ኮሚቴው በፀደቀበት ውሳኔ ላይ በተመለከተው መሠረት በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት ለአንድ ለተወሰነ ዘላቂ ዓላማ የሚውል ከሆነ ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅት ይቋቋማል።

፪/ በበጎ አድራጎት ኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብ ወይም ንብረት የታቀደውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነው እጅግ የበዛ ከሆነ የኮሚቴው አባላት በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅትነት ለመመዝገብ ሊያመለክቱ ይችላሉ።

፫/ ኮሚቴው በድርጅትነት ከተመዘገበ፣ በኮሚቴው የተሰበሰበው ገንዘብና ንብረት ወደተመዘገበው ዘላቂ በጎ አድራጎት ድርጅትነት ይተላለፋል።

**ንዑስ ክፍል ስድስት**

**ኅብረቶችና የኅብረቶች ኅብረት**

**፶፮/ ኅብረቶችና የኅብረቶች ኅብረት አመሠራረት**

፩/ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ወይም ኅብረቶች የጋራ ዓላማቸውን ለማሳካት በመካከላቸው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በዚህ ሕግ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ኅብረት ወይም የኅብረቶች ኅብረት መመሥረት ይችላሉ።

፪/ ኅብረቶች ወይም የኅብረቶች ኅብረት ከአባሎቻቸው መብትና ጥቅም ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ሕጋዊ ዓላማ ለማሳካት ሊመሠረቱ ይችላሉ፤ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል:-

ሀ) ለጋራ ግቦች ስኬታማነት አባሎቻቸውን ማስተባበርና መደገፍ፣

ለ) የሀሳብ፣ የመረጃ እና የልምድ ልውውጥን ማካሄድ፣

**55/ Change into a Charitable Endowment**

1/ Where under the decision approving the Charitable committee the money or property collected by the Charitable committee is to be destined to a specific lasting object, a Charitable Endowment shall be constituted for the attainment of such object.

2/ Where the money or property collected by the charitable committee is significantly larger than what is necessary for the attainment of the proposed purpose, the members of a Charitable committee may seek permission and apply to the Agency for registration as civil society organization.

3/ If the Committee is registered as an organization, the money or property collected by the Committee shall be transferred to the Charitable Endoment.

**SUB SECTION SIX**

**CONSORTIA AND CONSORTIUM OF CONSORTIUMS**

**56/ Formation of a Consortium and a Consortium of Consortiums**

1/ Two or more civil society organizations or consortiums may form a consortium or a consortium of consortiums in accordance with an agreement concluded among themselves towards the achievement of their objectives or in accordance with the provisions of this Proclamation.

2/ Consortiums or a consortium of consortiums may be established for any legal purpose related to rights and benefits of their members including those indicated below:

a) To support their members for the achievement of common objectives;

b) To facilitate the sharing of ideas, information and experience;

ሐ) የአባላትን አቅም መገንባትና ሀብት የማሰባሰብ ጥረታቸውን መደገፍ፣

መ) የአባላትን ሥነ ምግባርና የሙያ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን

ሠ) የአባላት የጋራ ድምፅ በመሆን የአባላትን የጋራ መብትና ጥቅም ማስከበር እና ለአባላት ምቹ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር መሟገት፣

ረ) አባሎቻቸው በተሠማሩበት የሥራ ዘርፍ የጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም የፖሊሲ ሙግት እና ድጋፍ ሥራዎችን ማከናወን፣

፫/ ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱት ዓላማዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም ኅብረት አባል ድርጅቱ ከሚሰራበት የሥራ ዘርፍ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሥራ በመሥራት ከአባሉ ጋር ውድድር ውስጥ ሊገባ አይችልም። ሆኖም፣ኅብረቶች ሀብት በማሰባሰብ በአባሎቻቸው አማካኝነት የፕሮጀክት ሥራዎችን ማከናወን ይችላሉ።

## ንዑስ ክፍል ሰባት
## የድርጅቶች ምዝገባ

### ፶፯/ ምዝገባ

፩/ ማንኛውም ድርጅት በዚህ ሕግ መሠረት በኤጀንሲው መመዝገብ አለበት።

፪/ ኤጀንሲው የአገር በቀል ድርጅት ማመልከቻ በቀረበለት በ፴ቀናት ውስጥ፣ የውጭ ድርጅት ከሆነ ደግሞ የምዝገባ ማመልከቻ ከሥራ እቅድ ጋር በቀረበለት በ፵፭ ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ የተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አመልካች ድርጅቱን በመመዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፫/ አመልካቹ ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያልተሰጠው እንደሆነ በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

c) To build the capacity of members and support their resource mobilization efforts;

d) To undertake activities designed to enhance the ethical and professional standards among members;

e) To work for the protection of the rights of members by articulating their common voice and advocate for enabling work environment for members;

f) To conduct research and policy advocacy activities in the sectors in which their members operate.

3/ Notwithstanding the above mentioned aims, a consortium may not involve itself in operations that place it in direct competition with a member organization. However, consortiums are not barred from collecting and mobilizing resources to operate projects through their member organizations.

## SUB SECTION SEVEN
## REGISTRATION OF ORGANIZATIONS

### 57/ Registration

1/ Any organizations shall be registered by the Agency in accordance with these provisions.

2/ The Agency shall, upon application and after ensuring the fulfillment of the requirements stipulated under this Proclamation, register the applicant and issue a registration certificate within 30 days from the date of application for local organizations and within 45 days for a foreign organization.

3/ Where the Agency fails to issue certificate of registration within the period indicated under sub-article 2, the applicant may file its complaint to the Board within 30 days from the expiry of such period.

፬/ ቦርዱ የቀረበለትን ቅሬታ በመመርመር በ፷ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፭/ ኤጀንሲው ድርጅቱን ያልመዘገበው ያለበቂ ምክንያት መሆኑን ቦርዱ ሲረዳ የምዝገባ ሰርተፊኬቱ ወዲያውኑ እንዲሰጥ ያዛል። ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም፣ ኤጀንሲው ለቀረበለት የምዝገባ ማመልከቻ በንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው ጊዜ ምላሽ ካልሰጠ፣ ድርጅቱን ላለመመዝገብ በቂ ምክንያት እንደሌለው ይቆጠራል።

፮/ በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አመልካች የቦርዱ ውሳኔ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል።

**፶፰/ ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶች**

፩/ የአገር በቀል ድርጅቶች የምዝገባ ማመልከቻ በድርጅቱ መሥራቾች ሰብሳቢ ተፈርሞ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች ማካተት ይኖርበታል:

ሀ) የመሥራቾችን ሥም፣ አድራሻና ዜግነት የያዘ የምሥረታ ቃለ-ጉባኤ፤

ለ) የመሥራቾች የመታወቂያ ወይም የፓስፖርት ኮፒ፤

ሐ) የድርጅቱን ሥም እንዲሁም ዓርማ (ካለው)፤

መ) የድርጅቱን ዓላማ እና ሊሰማራ ያሰበበትን የሥራ ዘርፍ፤

ሠ) ሊሰማራ ያሰበበትን የሥራ ቦታ (ክልል)፣

ረ) በመሥራቾች የፀደቀ መተዳደሪያ ደንብ፣

ሰ) የድርጅቱን አድራሻ።

፪/ በውጭ አገር የተመሰረተ ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገጉት አስፈላጊ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን ማቅረብ ይኖርበታል:-

4/ The Board shall examine the complaint and make a determination on the matter within a period of 60 (sixty) days.

5/ Where the Board finds that the Agency failed register the organization without a good cause, it shall direct the Agency to issue the certificate of registration forthwith. For the purpose of this provision, the Agency shall be deemed not to have a good cause to refuse registration if it fails to respond to such application within the time limit mentioned under sub article 2 of this article.

6/ An applicant dissatisfied with the decision of the Board may lodge an appeal before the Federal High Court within 30 days from receiving the Board's decision.

**58/ Documents Required for Registration**

1/ An application for registration by local organization shall be signed by the founders and contain the following particulars:

a) The minutes of the formative meeting indicating the names, addresses and citizenship of the founders;

b) Copy of the identity card or passport of the founders;

c) The name of the organization and its logo, if it has one;

d) The objectives of the organization and its intended sector of operation;

e) The region where it intends to operate;

f) The rules of the organization approved by the founders;

g) The organization's address;

2/ An application for registration of a foreign non-governmental organization shall, in addition to the conditions required under sub-article 1, be accompanied with the following documents:

ሀ) ድርጅቱ መቋቋሙን የሚያሳይ ከተቋቋመበት አገር የተሰጠው በአግባቡ የተረጋገጠ ሰነድ፣

ለ) ሥልጣን ያለው የድርጅቱ አካል ድርጅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰራ ያሳለፈው በአግባቡ የተረጋገጠ ውሳኔ፤

ሐ) በአገር ውስጥ ተወካዩ የተሠጠው በአግባቡ የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን፣ከተቋቋመበት ሀገር ኢምባሲ ወይም ኤምባሲ ከሌለ ከተቋቋመበት ሀገር ስልጣን ባለው አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ ወይም ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤

መ) ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ የሚተገበር የሥራ ዕቅድ።

፫/ የኅብረቶች የምዝገባ ማመልከቻ በተወካያቸው ድርጅት ኃላፊ አማካኝነት ተፈርሞ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ ይቀርባል፤

ሀ) በኅብረቱ መሥራች ድርጅቶች ተወካዮች የተፈረመ የመተዳደሪያ ደንብ፣

ለ) አባላት ኅብረቱን ለመመስረት የተስማሙበት ቃለ ጉባዔ፣

ሐ) ለኅብረቱ አባላት ከኤጀንሲው ወይም ሥልጣን ካለው የክልል አካል የተሰጠ የአባላት የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

፬/ አመልካቹ አግባብነት ባለው ደንብ የሚወስነውን የምዝገባ ክፍያ ይከፍላል።

፭/ የሙያ ማኅበራትን ምዝገባ እና አስተዳደር ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ቦርድ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

a) Duly authenticated certificate of registration showing its establishment from its country of origin;

b) Duly authenticated resolution of its competent organ to operate in Ethiopia;

c) Duly authenticated power of deligation of the country representative; Letter of recommendation from the embassy in which the charity is incorporated or in the absence of such by a competent authority in that country or from Ministry of Foreign affairs of federal democratic republic of Ethiopia and;

d) An action plan for a minimum period of two years.

3/ The application for registration by a consortium shall be signed and submitted by the head of their representative organization and shall contain the following particulars:

a) Rules of the consortium signed by the representatives of founder o;

b) The minutes of the decision among members to form the consortium;

c) A certificate of registration issued by the Agency or authorized regional government body to the members of the consortium.

4/ The applicant shall pay a registration fee to be determined by the relevant Regulation.

5/ The Civil Society Organizations Board may issue directives on details regarding the registration and administration of professional associations.

## ፶፱ የምዝገባ ጥያቄን ስላለመቀበል

፩/ ኤጀንሲው ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ መኖሩን ካረጋገጠ ድርጅቱን አይመዘግብም፡-

ሀ/ ማመልከቻው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፰ የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ ሆኖ ሲገኝና ይህንንም እንዲያስተካክል የአመልካቹ ተወካይ ተጠይቆ ለማስተካከል ካልቻለ፤

ለ/ የድርጅቱ ዓላማ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተመለከተው የሥራ ዝርዝር ለሕግ ወይም ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆነ፣

ሐ/ ድርጅቱ የሚመዘገብበት ሥም ወይም ዓርማ፣ ከሌላ ድርጅት ወይም ከማንኛውም ሌላ ተቋም ሥም ጋር የሚመሳሰል ከሆነ ወይም ሕግን ወይም የሕዝብን ሞራል የሚቃረን ከሆነ፣

መ/ ድርጅቱ ለምዝገባ ያቀረበው ሰነድ በሐሰት የተዘጋጀ ወይም የተጭበረበረ ከሆነ።

፪/ በዚህ ሕግ በግልጽ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ኤጀንሲው በአሰራርም ይሁን መመሪያ በማውጣት የምዝገባ ጥያቄን ሊከለክል አይችልም።

፫/ ማመልከቻውን በዚህ ሕግ መሠረት መርምሮ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ አመልካቹ የጎደለውን ነገር በ፴ ቀናት ውስጥ አስተካክሎ እንዲቀርብ ኤጀንሲው በጽሑፍ መልስ ይሰጠዋል።

፬/ አመልካቹ የተባለውን ነገር ለማስተካከል ፍቃደኛ ካልሆነ ኤጀንሲው ማመልከቻውን ያልተቀበለበትን ሕጋዊ ምክንያት በመጥቀስ ጥያቄውን ውድቅ ያደርጋል።

፭/ የምዝገባ ጥያቄው ውድቅ የሆነበት አመልካች በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን በ፴ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 59/ Refusal of Application for Registration

1/ The Agency shall refuse to register an organization where it finds that:

a) The application does not comply with the necessary conditions set out under Article 58 of this Proclamation and the applicant's representative fails to meet such conditions after being requested to do so;

b) The aim of the organization or the activities description under the organization's rules are contrary to law or public moral;

c) The name or symbol under which the proposed organization is to be registered resembles the name of another organization or any other institution or is contrary to public moral or is illegal;

d) The document furnished for registration by the organization is fraudulently obtained or forged.

2/ The Agency may not refuse applications for reasons other than those specified under this on the basis of practice or directive.

3/ If an application fails to fulfill the necessary requirements laid out under the law, the Agency must provide a written response permitting the applicant to fulfill such requirements and resubmit its application within 30 days.

4/ If the applicant is unwilling to amend and resubmit its application, the Agency shall reject the application for registration and state the legal grounds for rejecting the application.

5/ An applicant that is dissatisfied with the Agency's decision may lodge a complaint before the board within 30 days from receiving the decision.

፮/ ቦርዱ ቅሬታው በቀረበለት በ ፷ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፯/ አንድ ድርጅት በማታለል ወይም በማጭበርበር የምዝገባ የምስክር ወረቀት አግኝቶ ከሆነ፣ ይኸው በኤጀንሲው ሲረጋገጥ ቦርዱ ድርጅቱ እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል።

፰/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፮ እና ፯ መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ድርጅት የቦርዱ ውሳኔ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ይግባኙን በመሥራቾቹ አማካኝነት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

**፷/ የመተዳደሪያ ደንብ አስፈላጊነትና ይዘት**

፩/ ማንኛውም ድርጅት የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የመተዳደሪያ ደንብ ሊኖረው ይገባል፡-

ሀ) የድርጅቱ ሥም

ለ) የድርጅቱ ዓላማዎች፣

ሐ) የድርጅቱ የበላይ አካል፣ ሥልጣንና ተግባር፣ የውስጥ አደረጃጀትና አስተዳደር፣ የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት፣

መ) የድርጅቱ ገቢና ሐብት ለአባላት እንዲሁም ለሠራተኞች በሕግ ከተፈቀደ የአገልግሎት ክፍያ በቀር ሊከፋፈል የማይችል መሆኑን፣

ሠ) የድርጅቱ አባል ወይም ሠራተኛ በመሆኑ ብቻ በድርጅቱ ንብረት ላይ አንዳችም መብት የማይኖረው መሆኑን፣

ረ) ድርጅቱ ከአባላት የተለየ የራሱ መለያና የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑን፣

ሰ) የአባላት መለዋወጥ በድርጅቱ ሕልውና ላይ ተጽዕኖ የሌለው መሆኑን፣

ሸ) አባልነት በውርስ የማይተላለፍ መሆኑን፣

ቀ) የድርጅቱ የሒሳብና የገንዘብ እንቅስቃሴ ተቀባይነት

6) The Board shall review the compliant and give its decision with in 60 days up on reciving the compliant.

7) If an organization obtained a registration certeficate by fraudulent or forgery act and if it is verified by the Agency, the Board shall decide dissolussion of The Organization.

8/ If the organization is unsatisfied with the board's decision that is given in accordance with sub article 6 and 7 of this article, the organization may lodge an appeal before the Federal High Court within 30 days from receiving the board's decision.

**60/ The Significance of an Organizational Rule and Its Contents**

1/ All organizations must have rules containing the following:

a) The organization's name

b) The organization's objectives

c) The organization's executive body, power and functions, internal governance and structure, meeting and decision-making procedures

d) A stipulation indicating that the organization's income and resources may not be distributed to members or employees except for payment of legally permitted service fees;

e) A stipulation indicating that the organization's members or employees do not have an automatic right over the organizations resource only by the mere fact of their membership ;

f) A stipulation indicating that the organization has a separate and independent legal personality and symbol from its members;

g) A stipulation indicating that Change of Members of the organization do not have effect on the existence of the organization;

h/ Membership does not devolve by inheritance;

i/ The organization's accounts and financial transactions

ባለው የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት የሚመራ መሆኑን፣

በ) የድርጅቱን የሥራና የሒሳብ ዕቅድና አፈጻጸም የሚመረምረውና የሚያጸድቀው የበላይ አካል መሆኑን፣

ተ) መተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻልበትን ሥርዓት፣

ቸ) የድርጅቱን የበጀት ዓመት፣

ነ) ድርጅቱ እንዲፈርስ ወይም እንዲዘጋ የሚወስነውን የበላይ አካልና የሚመራበትን ሥርዓት፣

ኘ) ድርጅቱ ሲፈርስ ያለበትን ሕጋዊ ዕዳ ከፍሎ ተራፊው ንብረት የድርጅቱ የበላይ አካል ለመረጠው ሌላ ድርጅት ወይም በኤጀንሲው በኩል ለሌላ አካል ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት ለተቋቋመው ፈንድ የሚተላለፍ መሆኑን፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የመተዳደሪያ ደንቡ የሚከተሉትንም ሊያካትት ይችላል:-

ሀ) ለአባልነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፤

ለ) አባልነት የሚቋረጥባቸውን ወይም የሚታገድባቸውን ምክንያቶች፤

ሐ) አባልነት ሲቋረጥ ወይም ሲታገድ በድርጅቱ ውስጥ ይግባኝ የሚጠየቅበት ሥርዓት፣

መ) የአባልነትና ሌሎች ክፍያዎች የሚወሰኑበትና የሚጠየቁበት ሥርዓት፤

ሠ) የሥራ አመራር ኃላፊዎች የሚሾሙበትና የሚሻሩበት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራት፤

ረ) የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት የሚሾምበትና የተጠሪነት ሥርዓት፣ ሥልጣንና ተግባራት፤

ሰ) በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ የሚሰማራ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ፤

will be managed by an accepted accounting system;

j/ The supreme body of the organization will examine and approve the organization's financial and work plan and performance;

k/ Procedure for amending the rules;

l/ The organization's budget year;

m/ The organizational body that will decide to dissolve and close the organization, and the procedures to be followed;

n/ A stipulation indicating that during dissolution, once the debts of the organization are paid the outstanding money and property shall be transferred to another organization named by the organization's supreme body or to another body through the agency or to the fund established under this proclamation.

2/ In addition to the information mentioned above. the rules the organization may also include:

a) Requirements that must be fulfilled for membership

b) Reasons for termination or suspension of membership

c) Internal procedures for appealing from decisions to terminate or suspend membership;

d) Procedures for imposing and collecting membership and other fees;

e) The power, procedure for appointment and procedure for removal of executive members of the organization;

f) The powers and functions and procedure for the appointment and accountability of the officers of the organization;

g) Whether or not the organization performs fundraising activities ;

**፷፩/ <u>የምዝገባ ውጤት</u>**

በዚህ ሕግ የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ የተመዘገበ ድርጅት፡-

፩/ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፤

፪/ በሥሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ውል ይዋዋላል፤

፫/ ልዩ የሥራ ፈቃድን የሚመለከቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በማናቸውም ሕጋዊ የሥራ መስክ የመሰማራት መብት አለው፤

፬/ በሥሙ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት የመሆን፣ንብረት የማስተዳደርና የማስተላለፍ መብት አለው። ሆኖም ንብረቱም ሆነ ከንብረቱ ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ በስጦታ ለአባላት ጥቅም ወይም ከአላማው ውጪ ለሆነ ተግባር ሊተላለፍ አይችልም፤

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፬ መሰረት ንብረት ያስተላለፈ ድርጅት በ፲፭ የስራ ቀናት ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለበት፡፡

**፷፪/ <u>የሥራ ነፃነት</u>**

፩/ ማንኛውም ድርጅት የተቋቋመበትን ሕጋዊ ዓላማ ለማሳካት በየትኛውም ሕጋዊ ሥራ ላይ የመሠማራት ሙሉ መብት አለው።

፪/ አገር በቀል ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ለመሥራት፣ እንዲሁም አህጉራዊ፣ ክፍለ አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው ዓላማን ተግባራዊ ለማድረግ ይችላሉ።

፫/ ማንኛውም ድርጅት፣ በራሱ የፕሮጀክት ሥራን ለማከናወን ወይም ለሌሎች ድርጅቶች የገንዘብና የዕውቀት ድጋፍ ለማድረግ ሊቋቋም ይችላል።

፬/ ድርጅቶች የሚያከናውኗቸው ሥራዎች ጋር ግንኙነት ወይም ተያያዥነት ያላቸውን ፣ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች እንዲለወጡ፣ እንዲሻሻሉ ወይም አዲስ ሕጎችና ፖሊሲዎች እንዲወጡ ሐሳብ ማቅረብ ይችላሉ።

**61/ <u>Result of Registration</u>**

Any organization which registered upon fulfillment the registration requirements provided in this Proclamation:

1/ Shall have legal personality;

2/ Can sue, be sued and enter into contracts;

3/ Without prejudice to laws that require special license, can operate in the sector of its choice;

4/ To own, administer and transfer movable and immovable property. However, the proceeds from the disposal of the property may not be transferred as donation for the benefit of members or to another activity which is not its mission.

5/ The organization which transfer property based on sub article 4 of this article shall inform to the agency within 15 days.

**62/ <u>Operational Freedom</u>**

1/ An organization shall have the right to engage in any lawful activity to accomplish its objectives.

2/ Indigenous organizations shall have the right to operate in Ethiopia or abroad, or implement objectives having global, regional or sub regional nature.

3/ An organization may be established to implement project activities on its own or to provide financial and technical support to other organizations.

4/ The Organization may propose recommendations for the change or amendment of existing laws, policies or practices, or issuance of new laws and policies of those which have relationship with the activities they are performing.

፭/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፬ የተመለከተው ቢኖርም፣ የውጭ ድርጅቶች በሌላ ህግ ካልተፈቀደላቸው በስተቀር እና ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖሩ የውጪ ሀገር ዜጎች የተመሰረቱ ሀገር በቀል ድርጅቶች የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማግባባትም ሆነ ግፊት በማድረግ ተጽዕኖ መፍጠር፣ በመራጮች ትምህርት ወይም በምርጫ መታዘብ ሥራ ላይ መሰማራት አይችሉም።

፮/ የውጭ ድርጅቶች በራሳቸው የፕሮጀክት ሥራዎች ለማከናወን ወይም ከሌሎች መንግሥታዊ ካልሆኑ አገር በቀል ድርጅቶች ጋር የገንዘብ፣ የዓይነትና የዕውቀት ድጋፍ በማድረግ መሥራት ይችላሉ።

፯/ የውጭ ድርጅቶች በተቻለ መጠን ከአገር በቀል ድርጅቶች እና መንግስታዊ ድርጅቶች ጋር በአጋርነት በመሥራት የአገር በቀል ድርጅቶችን አቅም እንዲጎለብት ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ ።

፰/ ማንኛውም ድርጅት የሚያከናውናቸው ሥራዎች ዘላቂ ልማትን የሚያመጡና ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉ ወይም የአባላቶቹን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ወይም የተሰማሩበትን የሙያ መስክ ለማሳደግ አስተዋጽዖ ያለው እንዲሆን ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት።

፱/ ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም መሥራትን ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ድርጅት፣ የሴቶችን፣ ህጻናትን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአረጋውያንንና ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ ወይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥቅምን ማካተቱን ማረጋገጥ አለበት።

፲/ ማንኛውም ድርጅት ከተመዘገበ በኋላ በሌላ ሕግ የተለየ ፍቃድ እንደሚያስፈልጋቸው በተመለከቱ የሥራ ዓይነቶች ከሚመለከታቸው የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን ፈቃድ ሳያገኝ ወደሥራ መግባት አይችልም።

5/ Notwithstanding Sub Article (4) of this Article, unless it is permitted with an other law foreign organizations and local organizations which are established by foreign citizens which are residents of Ethiopia may not engage in lobbying political parties.

6/ Foreign organizations may implement project activities or work in partnership with local organizations by providing financial, technical or in kind support.

7/ To the extent possible, foreign organizations by working in partnership with local and governmental organizations, can give support to build the capacity of local organizations.

8/ Any organization shall make the necessary efforts to ensure that its activities help to bring about sustainable development, contribute to the democratization process, promote the rights and interests of its members or enhance the profession they are engaged in.

9/ An organization which is established for the benefit of the general public or third parties shall ensure that its activities take into account the interests of women, Children, persons with disabilities, the elderly and others exposed to threat or vulnerable groups of the society.

10/ Any organization cannot engage in sectors which require additional permit by law without getting the necessary permit from the relevant government bodies.

፲፩/ የማንኛውም ድርጅት አባል፣ አመራርና ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የድርጅቱን ጥቅም የማስቀደምና ከእነሱ ጥቅም ጋርም እንዳይጋጭ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

**፷፫/ <u>የሀብት አሰባሰብ እና አስተዳደር</u>**

፩/ ማናቸውም ድርጅት፡-

ሀ) ለሚተገብረው ፕሮጀክት ዘላቂነት አስፈላጊ በመሆናቸው፣ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ፕሮጀክቱ ከሚፈጸምበት ቦታ እንዳይወጡ በፕሮጀክት ስምምነቱ ላይ በግልጽ ከተመለከቱ ንብረቶች በስተቀር፣ ማንኛውም ድርጅት ንብረቱን ከአንድ ክልል ወደሌላ ክልል ወይም የከተማ አስተዳደር የማንቀሳቀስ ሙሉ መብት አለው።

ለ) ለዓላማው መሳካት ገቢ ለማግኘት በማንኛውም ሕጋዊ የንግድና ኢንቨስትመንት ሥራ ውስጥ አግባብነት ባላቸው የንግድና ኢንቨስትመንት ሕጎች መሠረት የመሳተፍ መብት አለው። ሆኖም ከሥራው የሚገኘውን ትርፍ ለአባላት ጥቅም ማስተላለፍ አይችልም።

ሐ) ለዓላማው መሳካት ከየትኛውም ሕጋዊ ምንጭ ገንዘብ የመጠየቅ፣ የመቀበልና የመጠቀም መብት አለው።

፪/ ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም መሥራትን ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ድርጅት፣ የአስተዳደር ወጪው ከገቢው ከ፳ በመቶ ሊበልጥ አይችልም። ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ‹‹**የአስተዳደር ወጪ**›› ማለት ድርጅቱ ከሚያከናውነው የፕሮጀክት ሥራ ጋር ተያያዥነት የሌለው፣ነገር ግን ለድርጅቱ ሕልውና ቀጣይነት አስፈላጊ የሆነ እና ከአስተዳደር ሥራዎች ጋር የተያያዘ ወጪ ሲሆን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማጥቅሞችን፣ ከአስተዳደር ሥራ ጋር የተያያዘ የአላቂና ቋሚ እቃዎች ግዢን፣ የጥገናና እድሳት ወጪዎችን፣የቢሮ ኪራይ፣የፓርኪንግ ክፍያዎች፣ የኦዲት አገልግሎት፣ የማስታወቂያ ክፍያ፣ የባንክ አገልግሎት፣የመብራት፣የስልክ፣ የፋክስ፣ የውሃ፣

11/ In performing their duties all members, officers and employees of the organization have the responsibility to give primacy to the organization's interest and take the necessary precaution to avoid conflict of interest.

**63/ <u>Resource Mobilization and Administration</u>**

1. Any Organization:

a) Shall have the right to move its properties from one region to another region or city administration, unless the Project Agreement states that such properties may not be transferred because they are necessary for the sustainability of a specific project it is implementing.

b) Have the right to engage in any lawful business and investment activity in accordance with the relevant trade and investment laws in order to raise funds for the fulfillment its objectives. However, the profit to be obtained from such activities may not be transferred for the benefit of members.

c) Shall have the right to solicit, receive and utilize funds from any legal source to attain its objective.

2/ The Administrative cost of an organization established for the benefit of the general public or that of third Parties may not exceed twenty percent of its total income. For the purpose of this provision, "**Administrative Expense"** shall mean expenses which are not related to the project activities of an organization but are necessary to ensure the continuity of an organization and related to administrative activities, and shall include: salaries and benefits of administrative employees; purchase of consumables and fixed assets and repair and maintenance expenses related to administrative matters; office rent, parking fees, audit fees, advertisement expenses, bank service fees, fees for electricity, fax, water and internet services; postal and

ኢንተርኔት፣ የፖስታና የሕትመት አገልግሎት ወጪዎችን፣ ታክስ፣ ለአስተዳደር ሥራ የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ግዢ፤ ጥገና፤ የነዳጅና ዘይት እንዲሁም የመድኅን ግዢ ወጪዎችን፣ የቅጣት ክፍያዎችን፣ እንዲሁም የጥብቅና አገልግሎት ክፍያን ያካትታል።

፫/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከተው ድንጋጌ በልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ የማይሆንባቸውን ድርጅቶች በሚመለከት ኤጀንሲው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፷፬/ <u>በገቢ ማስገኛ ስራዎች ስለመሠማራት</u>**

፩/ ከላይ በአንቀጽ ፷፫ (፩)(ለ) መሠረት በገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ የሚሰማራ ድርጅት፣ አግባብነት ባላቸው የንግድ ፈቃድና ምዝገባ ህጎች መሠረት፣ አዲስ የንግድ ድርጅቶችን (ኩባንያዎችን) በማቋቋም፣ በነባር የንግድ ድርጅቶች ውስጥ አክሲዮን በመያዝ ህዝባዊ መዋጮ መሰብሰብ ፣ ወይም የንግድ ስራን በብቸኛ ባለቤትነት በማካሔድ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን ማከናወን ይችላል፡፡

፪/ ድርጅቱ በራሱ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በሚያከናወንበት ጊዜ ለዚሁ ስራ የተለየ የባንክ ሒሳብ መክፈት፣ እንዲሁም በንግድ እና ታክስ ህጉ በሚጠየቀው መሠረት የገቢ ማስገኛ ስራውን የሚመለከት የተለየ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል፡፡

፫/ አግባብነት ያላቸው የታክስ፣ የንግድ ፈቃድና ምዝገባ፣ እንዲሁም የአንቨስትመንት ሕጎች በገቢ ማስገኛ ስራዎችን በመሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፬/ ድርጅቱ ከገቢ ማስገኛ ስራው የሚያገኘው ገቢ፣ የድርጅቱን የአስተዳደር እና የፕሮገራም ወጪዎች ለመሸፈን ይውላል፡፡

፭/ ድርጅቱ ከገቢ ማስገኛ ስራው የሚያገኘው ገቢና ሃብት ለአባላት እንዲሁም ለሠራተኞች ሊከፋፈል አይችልም።

printing expenses; tax, purchase and repair of vehicles for administrative purposes, and procurement of oil and lubricants for the same; insurance costs, penalties and attorney fees.

3/ The Agency may issue directives regarding organizations exempted from the application of provisions of sub Article 2 of this Article.

**64/ <u>Income Generation Activities</u>**

1/ An organization which engages in income generating activities in accordance with Article 63(1)(b) of this Proclamation may do so by establishing a separate business organization (company), acquiring shares in an existing company, collect public collections or operating its business as a sole proprietorship.

2/ An organization engaged in income generating activities shall open a separate bank account and keep separate books of account for its business in accordance with the relevant commercial and tax laws.

3/ The relevant tax, commercial registration and business licensing, and investment laws shall be applicable to income generation activities under this provision.

4/ Income that is generated from income generating activities will be used to cover administrative and program costs of the organization.

5/ The income and resources that are acquired from income generating activities shall not be transferred or shared for the benefit of members or workers of the organization.

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሰረት ድርጅቶች ህዝባዊ መዋጮ ሲሰበስቡ ለኤጀንሲው ማሳወቅ አለባቸው፤

፯/ በዚህ አንቀፅ መሰረት በገቢ ማስገኛ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ለኤጀንሲው በአስራ አምስት የስራ ቀናት ማሳወቅ አለበት ፡፡

**፷፭/ በሥራ መሪነት ወይም በቦርድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት መሥራት የማይችሉ ሰዎች**

፩/ ማንኛውም ሰው በአንድ ድርጅት ውስጥ በሥራ መሪነት ወይም በድርጅቱ የቦርድ/ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት መሥራት የማይችለው:-

ሀ) በማታለል ወይም ታማኝነትን በማጓደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተቀጣና ያልተሰየመ ከሆነ፤

ለ) በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የሲቪል መብቱን የተገፈፈና መብቶቹ ያልተመለሱለት ከሆነ፣

ሐ) በሕግ መሠረት ከችሎታ ማጣት የተነሳ መሥራት የማይችል ከሆነ፣

መ) በፍርድ ቤት ክልከላ የተደረገበት ከሆነ ነው።

፪/ ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የማናቸውም ድርጅት የቦርድ ወይም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ሰው በዚያው ድርጅት ውስጥ የሥራ መሪ ወይም ተቀጣሪ ሠራተኛ ሆኖ መሥራት አይችልም።

፫/ የድርጅቱ የምዝገባ ማመልከቻ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በመጣስ የቀረበ ከሆነ ኤጀንሲው ድርጅቱን አይመዘግብም።

**፷፮/ የድርጅቶች መዝገብ**

፩/ ኤጀንሲው ድርጅቶች የሚመዘገቡበት መዝገብ ይይዛል።

፪/ በኤጀንሲው ትክክለኛ ቅጂ ስለመሆኑ የተረጋገጠ የመዝገቡ ሙሉ ወይም ከፊል ግልባጭ በማናቸውም

6/ when the organizations collect public collections based on sub article 1 of this article, they shall inform to the agency.

7/ An organizations engaged in income generating activities based on this Article shall inform to the Agency within fifteen days.

**65/ Persons Who shall not Act as Officer or Board Management Committee Member**

1/ No person shall act as an Officer or Board Management Committee Member of an Organization or a branch thereof if that person:

a) has been convicted of a crime that involves fraud or other crimes that involve dishonest acts and has not been reinstated;

b) has been convicted of any crime as a result of which she/he has been deprived of his civil rights and his civil rights have not yet been restored;

c) Is unable to act by reason of incapacity within the meaning of law;

d) Has been interdicted by a court.

2/ In addition to the restrictions laid out under sub-article 1, a member of the board or executive committee of an organization shall not be employed in the same organization as an officer or ordinary employee.

3/ If the application for registaration that is submitted by the Organization is contrary to the rules stated under sub Article 1 and 2 of this Article the Agency shall not register the Organization.

**66/ Register of Organizations**

1/ The Agency shall keep a register of Organizations.

2/ A copy of or extract from any such document certified to be a true copy or extract under the seal of the Agency

የክርክር ሂደቶች በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል።

፫/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡትን እንዲሁም የታገዱትንና ከመዝገብ የተሠረዙትን ድርጅቶች ዝርዝር በየስድስት ወሩ በጋዜጣ ያወጣል።

**፷፯ የድርጅት ቅርንጫፍ**

፩/ ማንኛውም ድርጅት አስቀድሞ ለኤጀንሲው በማሳወቅ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚከፈት ቅርንጫፍ የሚሰጠው ሥልጣን ራሱን የቻለ ድርጅት የሚያደርገው ወይም ዋናው መስሪያ ቤት በቂ ቁጥጥር እንዳያደርግበት የሚከለክል ሊሆን አይችልም።

**፷፰. ለውጥን ስለማሳወቅ**

፩/ ማንኛውም ድርጅት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ለውጥ ሲያደርግ ለኤጀንሲው ማሳወቅና ማስመዝገብ አለበት፡

ሀ) የሥያሜ ወይም የምልክት ለውጥ፣

ለ) የሥራ ዘርፍ ለውጥ፣

ሐ) የዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ ለውጥ፣

መ) የሥራ ክልል ለውጥ፣

ሠ) የሥራ አመራር አባላትና የሥራ መሪ ለውጥ፣

ረ) በመተዳደሪያ ደንብ ላይ የሚደረግ ማናቸውም ለውጥ፣

ሰ) የባንክ ሒሳብ ወይም ፈራሚዎች ለውጥ፣

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የተደረገ ለውጥ የድርጅቱን ማናቸውም መብቶች ወይም ግዴታዎች አይነካም።

**፷፱/ የምስክር ወረቀትን በይፋ ስለማሳየት**

ማንኛውም ድርጅት የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በዋናው መስሪያ ቤት፣ እንዲሁም ግልባጩን በየቅርንጫፎቹ ለማናቸውም ጎብኚ ሊታይ በሚችል ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል። በተጨማሪም የድርጅቱ ሥምና መለያ ምልክት በድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሕዝብ ሊታይ በሚችል ግልጽ ስፍራ መቀመጥ ይኖርበታል።

shall be admissible in evidence in any proceedings.

3/ The Agency shall every six months publish in an official Gazzette the list of Organization registered, suspended or cancelled under this Proclamation.

**67/ Branch of an Organization**

1/ An organization may establish a branch based on its rules by giving prior notice to the Agency.

2/ The powers of the branch of the organization established under Sub-article (1) of this Article shall not make it an independent organization on its own or prevent the head office from making sufficient control on the branch.

**68/ Obligation to inform Changes**

If an organization makes changes to any of the following matters, it shall inform the agency about the change or amendment and get it registered.

a) Its name or symbol,

b) Change of organization’s operational sector,

c) Change of Headquarters,

d) Change the region of operation,

e) Change of executive members or chief executive,

f) Amendments of its rules,

g) Change of bank account or signatories.

2/ A change of name by an Organization under this Article shall not affect any rights or obligations of the Organization.

**69/ Display of Certificate**

Every organization shall keep its certificate of registration in its Head Office and a copy thereof in its branches in a place that is visible to any visitor. Additionally, the symbol and name of the organization must be placed at a publicly visible place at both the head office and the branch offices.

**፸/ ሕልውናን ስለማረጋገጥ**

፩/ ማንኛውም ድርጅት በዚህ አዋጅ ውስጥ ሪፖርት ለማቅረብ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ባለፈ በሦስት ወራት ውስጥ ሪፖርት ካላቀረበ ኤጀንሲው የድርጅቱን ሕልውና ለማረጋገጥ በጋዜጣ ጥሪ ያደርጋል።

፪/ ከላይ የተመለከተው ጥሪ በጋዜጣ በወጣ በ፴ ቀናት ውስጥ ድርጅቱ በርግጥም ሕልውና ያለው ከሆነ የድርጅቱ ሕጋዊ ተወካይ ቀርቦ በዚህ ሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያላቀረበበትን ምክንያት ማስረዳት ይጠበቅበታል።ተወካዩ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ድርጅቱ ሪፖርት ያላደረገበትን በቂ ምክንያት ካላቀረበ ዋና ዳይሬክተሩ ጉዳዩን ለቦርዱ አቅርቦ ድርጅቱ እንዲፈርስ ያስወስናል።

**ክፍል አራት**
**ሒሳብና ሪፖርት**

**፸፩/ የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ**

፩/ ማናቸውም ድርጅት የድርጅቱን የገንዘብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ተቀባይነት ባለው የሒሳብ አሰራር የተዘጋጀ የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት።

፪/ የሒሳብ ሰነዶቹ የድርጅቱን ገቢና ያወጣውን ወጪ፣ የወጪውን ምክንያት፣ ሐብትና ዕዳ፣ የለጋሾችን ማንነትና የገቢውን ምንጭ ያካተቱ መሆን አለባቸው።

፫/ ድርጅቱ የሥራ መሪዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት የተዘጋጁ የሒሳብ ሰነዶችን፣ የሒሳብ ዓመቱ ካለቀ በኋላ ቢያንስ ለአምስት ዓመት ጠብቀው የማቆየት ግዴታ አለባቸው።

**70/ Verification of Existence**

1/ If an organization fails to provide its report within 3 months from the expiry of the timeframe set under this Proclamation for submission of reports , the Agency will issue a notice in the gazette to verify its existence.

2/ If the organization does indeed maintain existence, the legal representative must be present to explain the situation within 30 days from the publication of the notice. However, if the representative falls to do so, the Director General shall submit the issue to the Board for the decision of dissolution of the Organization.

**SECTION FOUR**
**ACCOUNTS AND REPORT**

**71/ Duty to Keep Accounting Records**

1/ Any organization shall keep books of account that show the financial transactions in the organization and are prepared in accordance with acceptable accounting standards.

2/ The books of account shall contain entries showing from day to day all sums of money received and expended by the Organization, the matters in respect of which the receipt and expenditure takes place, name and identity of donors, source of donations; and record of the assets and liabilities of the Organization.

3/ The officers of an organization shall preserve any accounting records made for the purposes of this Article for at least 5 years from the end of the financial year of the Organization in which they are made.

**፸፪/ ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫና ምርመራ**

፩/ ማንኛውም ድርጅት ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሠረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫ ለኤጀንሲው በአድራሻው መላክ አለበት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ቢኖርም፣ በበጀት አመቱ ከሁለት መቶ ሺህ ብር የማይበልጥ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ድርጅት ገቢን፣ ወጪን፣ ሐብትና ዕዳን የሚያመለክት መግለጫ ብቻ ማቅረብ ይችላል።

፫/ ከላይ በንዑስ ቁጥር ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ድርጅት ሒሳብ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ ፫ ወራት ውስጥ በተመሰከረለት ኦዲተር መመርመር አለበት።

፬/ አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የድርጅቱ አባላት ወይም ለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከድርጅቱ ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ያላቸው መንግስታዊ አካላት የሒሳብ ምርመራ እንዲደረግ ከጠየቁ ኤጀንሲው የድርጅቱ ሒሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ሊያዝ ይችላል።

፭/ የድርጅቱ ሒሳብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በአምስት ወራት ውስጥ ካልተመረመረ እና ይህንን ለመፈጸም ድርጅቱ ፈቃደኛ ካልሆነ ኤጀንሲው የውጭ ኦዲተር ሾሞ ማስመርመር ይችላል።

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ እና ፭ መሠረት በኤጀንሲው በተሾመው ኦዲተር ለተከናወኑ ማናቸውም የኦዲት ሥራዎች ወጪ የሚከፍለው የሚመለከተው ድርጅት ወይም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ የሥራ መሪዎቹ ይሆናሉ።

**፸፫/ ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት**

፩/ የሥራ መሪዎች የድርጅቱን የእያንዳንዱን የበጀት ዓመት ዋና ዋና ክንዋኔዎች የሚያሳይ ሪፖርት የሒሳብ ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው

**72/ Annual Statements of Accounts and Examination of Account**

1/ Any Organization shall submit to the Agency an annual statement of accounts prepared in accordance with acceptable standards.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, Organizations whose annual flow of funds does not exceed Birr 200,000.00, (two hundred thousand) the statement of accounts may choose to only prepare a receipts and payments account and a statement of assets and liabilities.

3/ With the exception to the stipulations under Sub-article (2), all Organizations' account shall be examined annually by a Certified Auditor within three months after the end of the financial year.

4/ If one third of the organization's members, donors or governmental bodies that have requested the examination of accounts, the Agency may appoint a certified external auditor.

5/ Where it appears to the Agency that the account of an Organization is not audited within five months from the end of that year and the Organization is unwilling to have it audited, the Agency may appoint a certified external auditor.

6/ In accordance with Sub-article (4) and (5) of this Article, the expenses of any audit carried out by an Auditor appointed by the Agency shall be paid by the Charity or Society concerned, or by its officers if the latter are found to be at fault.

**73/ Annual Activity Report**

1/ The officers of an organization shall prepare and submit to the Agency every Budget year major activity reports regarding the organization with in three months up on the

ማቅረብ አለባቸው።

፪/ ማንኛውም የሥራ ክንውን ሪፖርት ለኤጀንሲው ሲቀርብ የሒሳብ መግለጫ አብሮ መያያዝ አለበት።

፫/ ኤጀንሲው የቀረበለትን ሪፖርት በመመርመር ድርጅቱ ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ማብራሪያ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል።

**፸፬/ ዓመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ክፍት ስለማድረግ**

፩/ በኤጀንሲው ዘንድ የሚገኝ ማናቸውም የድርጅት ዓመታዊ ሪፖርት ወይም ሌላ ሰነድ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ወይም በድርጅቱ አባላት ሲጠየቅ በማናቸውም አመቺ ጊዜ ክፍት መደረግ አለበት።

፪/ ማናቸውም ድርጅት ዓመታዊ የሥራ ክንውን እና የኦዲት ሪፖርቱን ለአባላቱና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ አለበት።

**፸፭/ የባንክ ሒሳብ ስለመክፈት**

፩/ ማንኛውም ድርጅት የባንክ ሒሳብ ለመክፈት በቅድሚያ ከኤጀንሲው በጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት። ኤጀንሲው የባንክ ሒሳብ ለመክፈት ጥያቄ በቀረበለት በ ፭ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

፪/ የማንኛውም ድርጅት የገንዘብ እንቅስቃሴ በስሙ በተከፈተ የባንክ ሒሳብ መከናወን ይኖርበታል።

፫/ ማንኛውም ባንክ ኤጀንሲው በጠየቀ ጊዜ ወዲያውኑ በማናቸውም የድርጅት ሥም የተከፈቱ የባንክ ሂሳቦችን ዝርዝርና የሒሳብ መግለጫዎችን የመስጠት ግዴታ አለበት።

፬/ የድርጅት የባንክ ሒሳብ እንቅስቃሴ በመተዳደሪያ ደንቡ በተመለከተው አኳኋን ነው።

**፸፮/ የውጭ ዜጎችን ስለመቅጠር**

፩/ ማንኛውም ድርጅት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሥራ ፈቃድ ያልተሰጠውን የውጭ ዜጋ መቅጠር አይችልም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ ቢኖርም የውጭ ድርጅት የውጭ አገር ዜጋን የአገር ውስጥ ተወካይ አድርጎ ለመመደብ ገደብ አይኖርበትም።

end the Budget year.

2/ Every such annual activity report shall have attached to it the annual statement of accounts.

3/ After reviewing the reports the Agency may require additional information or explanation.

**74/ Disclosure of Annual Activity Report to the Public**

1/ Any annual activity report or other document kept by the Agency, when requested by any concerned body or members of the organization, must be made open to the public at any given time.

2/ All organizations must make available at all times, to their beneficiaries and members, the books of account, audit reports and annual reports.

**75/ Opening a Bank Account**

1/ An organization shall get a written approval of the Agency to open a bank account. The Agency shall respond to requests for such approval within five days from receipt of the request.

2/ All financial transactions shall be performed through a bank account opened by an organization in its name.

3/ All banks have the obligation to provide the bank statement of accounts held by any organization to the Agency when requested.

4/ The Bank Account transaction can be done in the context of the organization rules.

**76/ Employing Foreigners**

1/ No organization may employ a foreign national who is not given work permit under the relevant laws.

2/ Notwithstanding the stipulation under sub-article 1, a foreign organization shall not be barred from appointing a foreign national as its country

፫/ ከአገር ውስጥ ተወካዩ በስተቀር ሌሎች የውጭ አገር ዜጎች በድርጅቱ ሊቀጠሩ የሚችሉት ሥራው በኢትዮጵያውያን ሊከናወን የማይችል ስለመሆኑ በሥራ ፈቃድ ሰጪው መሥሪያ ቤት ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፬/ በድርጅቱ መደበኛ ደመወዝ ሳይከፈላቸው በሙያቸው በበጎ ፈቃደኝነት ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ለማገልገል የሚመጡ የውጭ አገር ዜጎችን በሚመለከት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ ተፈጻሚ አይሆንም።

## ክፍል አምስት
## ሕግን ስለማስከበር

### ፸፯/ ምርመራ የማድረግ ሥልጣን

፩/ ከመንግሥት አካላት፣ ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ከሕዝብ ከሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ኤጀንሲው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ከሚገኙ መረጃዎች በመነሳት ማናቸውም ድርጅት ሥራውን በሕግ መሠረት እየሰራ ስለመሆኑ ኤጀንሲው ምርመራ ሊያደርግ ይችላል።

፪/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው ቢኖርም ኤጀንሲው ምርመራ ለማድረግ ሲወስን ምርመራውን ለማከናወን በቂ ምክንያት መኖሩን በቅድሚያ ማረጋገጥ አለበት።

፫/ የምርመራ ሥራዎች በተቻለ ፍጥነት በአጭር ጊዜ እንዲጠናቀቁና የድርጅቱን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና ሕልውና አደጋ ላይ እንዳይጥሉ ኤጀንሲው ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ አለበት።

፬/ ኤጀንሲው የምርመራ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት፣ ከባድ የሕግ ጥሰት መፈጸሙን ሲያረጋግጥና በዚህ ምክንያትም የድርጅቱ እንቅስቃሴ ማገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፣ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ የዕገዳ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል:: ሆኖም ቦርዱ በሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ እገዳው ቀሪ ይሆናል ።

representative.

3/ Foreign nationals other than the country representative may only be hired if the office granting work permit verifies that the work cannot be performed by Ethiopians.

4/ The provisions of sub article 3 shall not apply to foreign nationals who are not salaried employees but come to Ethiopia to professionally contribute by working as volunteers for a period not exceeding one year.

## SECTION FIVE
## LAW ENFORCEMENT

### 77/ Power of Inspection

1/ The Agency may conduct an investigation into the activities of an organization to check whether it is carrying on its activities in accordance with the law. The investigation shall be launched on the basis of information the Agency obtained from government organs, donors or the public, as well as information obtained by the Agency during the performance of its work.

2/ Notwithstanding the fulfillment of the conditions under sub-article 1, the Agency shall first ensure that it has sufficient reason to conduct the investigation.

3/ The Agency must take all precautionary measures to ensure that the investigation is performed within a short period of time and is not carried out in a way that hampers the day to day activities and continued existence of the organization.

4/ If, during the course of the investigation, the Agency finds that a grave violation of the law has been committed and such violation makes it necessary to suspend the activities of the organization, the Director of the Agency may give a suspension order for a period not exceeding three months. but if the board did not decided with in three month, the suspension shall seize to exist.

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት ዋና ዳይሬክተሩ በሰጠው እግድ ላይ ድርጅቱ በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ የሚችል ሲሆን፣ በቦርዱ ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ድርጅቱ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ ይችላል።

## ፸፰/ አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

፩/ ይህን አዋጅ እና ሌሎች ሕጎችን ለሚጥሱ ድርጅቶች ኤጀንሲው ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ ይችላል።

፪/ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ በፅሑፍ ሆኖ፣ የተፈጸመውን የሕግ ጥሰት፣ ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ እና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መስተካከል እንዳለበት በግልጽ ማሳየት አለበት። ኤጀንሲው ለማስተካከያ የሚሰጠው ጊዜ የተፈጸመውን ጉድለት ወይም ጥፋት ክብደትና የጉዳዩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

፫/ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ማስተካከያ የማያደርግ ከሆነ ወይም ድርጅቱ የፈጸመው ጥፋት ከባድ መሆኑን ኤጀንሲው ሲያምንበት ለድርጅቱ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

፬/ በተሰጠው ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መሠረት ድርጅቱ አሰራሩን የማያስተካክል ከሆነ ድርጀቱ እንዲታገድ ዋና ዳይሬክተሩ ሊወስን ይችላል። የዋና ዳይሬክተሩ ውሳኔ በቦርዱ ካልተነሳ ወይም በፍርድ ቤት ካልታገደ በቀር፣ የዕገዳ ውሳኔው በተሰጠ በሦስት ወራት ውስጥ ማስተካከያ ያላደረገ ድርጅት እንዲፈርስ ቦርዱ ይወስናል።

፭/ በቦርዱ የመፍረስ ውሳኔ የተሰጠበት ድርጅት አባላት፣ መሥራቾች ወይም ኃላፊዎች ውሳኔው በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ።

5/ Based on Sub Article 4 of this Article The organization may appeal to the Board on the decision of Director General within 30 days. The organization may appeal to the Federal High Court on the decision of the Board within 30 days after the board gave its decision.

## 78/ Administrative Measures

1/ The Agency may give warning to organizations that do not comply with this proclamation or other laws.

2/ The warning must be in writing and shall specify the violation, the measures to be taken and the time frame to rectify the violation. Such time frame shall take into account the gravity of the violation and the complexity of the case.

3/ If the fault committed by the organization is grave or the organization fails to redress its fault after being given clear warning, the Agency will give the organization a strict warning.

4/ The Director General of the Agency may order the suspension of the organization if the organization fails to alter or rectify its practice after receiving a strict warning. The Board will decide that an organization which failed to make the necessary rectifications within three months following the suspension order shall be dissolved unless the Director General's suspension order has been lifted by the Board or is blocked by court order.

5/ The Members, Founders or Managers of the Organization that is dissolved by the decision of the Board can appeal to Federal High court with in 30 days following the decision.

፮/ በድርጅቱ የተፈጸመው ሕግ የመተላለፍ ተግባር በወንጀል የሚያስጠይቅ ሲሆን ኤጀንሲው ጉዳዩን ሥልጣን ላለው የፖሊስ ወይም የዐቃቤ ሕግ ተቋም ይመራል።

**፸፱/ የመሰማት መብት**

ኤጀንሲው በማንኛውም ድርጅት ላይ የትኛውንም ዓይነት አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ድርጅቱ መከራከሪያዎቹንና ማስረጃዎቹን የማቅረብና የመሰማት መብት አለው።

**ክፍል ስድስት**
**ስለ ድርጅቶች መዋሐድ፣መከፋፈል እና መለወጥ**

**፹/ መዋሐድ**

፩/ ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ድርጅቶች አግባብነት ባላቸው ሕጎችና በመተዳደሪያ ደንባቸው መሠረት በአዲስ ስም ወይም ከሚዋሐዱት ድርጅቶች በአንዱ ስም ሊዋሐዱ ይችላሉ።

፪/ ውሕደቱ ሲፈጸም የቀድሞዎቹ ድርጅቶች መብትና ግዴታዎች እንዲሁም በውስጣቸው የነበሩ ሰራተኞች እንደአግባብነታቸው በውህደት ወደተፈጠረው ድርጅት ይተላለፋሉ።

፫/ በውሕደቱ የተፈጠረው አዲስ ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለበት።

**፹፩/ መከፋፈል**

፩/ አንድ ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተመለከተው መሠረት በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ሊከፋፈል ይችላል።

፪/ በመከፋፈሉ ውሳኔ ላይ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር፣ በክፍፍሉ የተፈጠረው እያንዳንዱ ድርጅት የቀድሞው ድርጅት ላለበት ግዴታና መብት እኩል ተካፋይ ነው።

6/ If the violation committed by the organization entails criminal responsibility, the Agency will direct the case to the competent body of the police or public prosecutor.

**79/ The Right to be Heard**

Any organization has the right to be heard and present its arguments before the Agency imposes any administrative measure.

**SECTION SIX**
**MERGER, DIVISION AND CONVERSION OF ORGANIZATIONS**

**80/ Merger**

1/ Two or more organizations may merge into one under a new name or under the name of one of the organizations in accordance with relevant laws and in accordance with their rules.

2/ The rights and obligations of the former organizations and based on their relevancy the Employees of those organizations shall be transferred to the newly formed organization.

3/ The newly established organization shall be registered in accordance with this Proclamation.

**81/ Division**

1/ An organization may be divided into two or more organizations upon the decision of its supreme organ in accordance with its rules.

2/ Unless stated otherwise in the decision to divide the organization, the organizations that result from the division shall bear the obligations and utilize the rights equally.

፫/ የቀድሞው ድርጅት ህልውና የሚያበቃው ለአዲሶቹ ድርጅቶች የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሲሰጥ ነው።

፬/ በአዲሶቹ ድርጅቶች ሙሉ ስምምነት ከነሱ አንዱ የቀድሞውን ድርጅት ስም ይዞ ሊቆይ ይችላል።

**፹፪/ መለወጥ**

፩/ አንድ ድርጅት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተመለከተው መሠረት በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ወደሌላ ዓይነት ድርጅት ሊለወጥ ይችላል።

፪/ ለውጡ ሲፈጸም የቀድሞው ድርጅት መብትና ግዴታዎች ፤እንዲሁም በውስጣቸው የነበሩ ሰራተኞች እንደአግባብነታቸው ወደተለወጠው ድርጅት ይተላለፋሉ።

፫/ የተለወጠው አዲስ ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና መመዝገብ አለበት።

## ክፍል ሰባት
## ስለድርጅቶች መፍረስ

**፹፫/ የድርጅቶች መፍረስ**

፩/ አንድ ድርጅት የሚፈርሰው፣

ሀ) በመተዳደሪያ ደንቡ ሥልጣን ባለው አካል እንዲፈርስ ሲወሰን፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸ ወይም ፸፰(፬) መሠረት ድርጅቱ እንዲፈርስ በኤጀንሲው ቦርድ ሲወሰን፤ወይም

ሐ) በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ነው።

፪/ ፍርድ ቤት አንድ ድርጅት እንዲፈርስ የሚወስነው፡-

ሀ) ድርጅቱ በከባድ የወንጀል ድርጊት ወይም በተደጋጋሚ በቀላል ወንጀል በመሳተፍ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፣ ወይም

ለ) ዕዳውን የመክፈል ችሎታ የሌለው ሲሆን ብቻ ነው።

3/ The existence of the former organization shall cease at the time when the certificates of registration are issued to the new organizations.

4/ With the unanimous consent of all newly formed organizations, one of the newly formed organizations may retain the name of the previous organization.

**82/ Conversion**

1/ Any organization may be converted into another form of organization where its Supreme organ so decides in accordance with its rules.

2/ The rights and obligations of the former organization and based on their relevancy the servants of those organizations shall be transferred to the organization after the conversion.

3/ The converted organization shall be registered again in accordance with this Proclamation.

## SECTION SEVEN
## DISSOLUTION OF ORGANIZATIONS

**83/ Dissolution**

1/ An organization may only be dissolved upon the decision of:

a) the Organization's competent organ in accordance with its rules;

b) the Board of the Agency when it idecides that the organization shall be dissolved in accordance with Article 70 or 78(4) of this Proclamation;

c) The Federal High Court.

2/ A court can dissolve an organization when;

a) It is convicted of a serious criminal offence or is repeatedly found guilty of a minor criminal offence; or

b) The organization is insolvent.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) መሠረት በአባላት ውሳኔ የፈረሰ ድርጅት ውሳኔውን ለኤጀንሲው በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ፫ መሠረት ድርጅቱ ለኤጀንሲው የሚያቀርበው ማስታወቂያ፣ ድርጅቱ እንዲፈርስ የተወሰነበትን ቃለ ጉባኤ፣ የድርጅቱን ወቅታዊ የሥራ ክንውንና የሒሳብ መግለጫ አያይዞ ማቅረብ አለበት።

**፹፬/ የመፍረስ ውጤት**

፩/ በአንቀጽ ፹፫ መሠረት ድርጅቱ እንዲፈርስ ሲወሰን ንብረቱ ወዲያውኑ በኤጀንሲው በሚሾም ሒሳብ አጣሪ ኃላፊነት ሥር ይሆናል።

፪/ ሒሳብ አጣሪው፣ ከድርጅቱ ዓላማ ጋር የተያያዙና ሊቋረጡ የማይችሉ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ካልሆነ በስተቀር ከሒሳብ ማጣራት ውጪ ሌላ ተግባር ማከናወን አይችልም።

፫/ የድርጅቱን ዕዳዎችና የማፍረስ ሂደቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ወጪዎች ተጠናቀው ከተከፈሉ በኋላ ሒሳብ አጣሪው የድርጅቱ ቀሪ ገንዘብ ወይም ንብረት በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል አስቀድሞ በተወሰነው መሠረት ለሌላ ድርጅት እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም በድርጅቱ የበላይ አካል ውሳኔ ላይ ካልተመለከተ ቀሪ ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ኤጀንሲው በሚወስነው መሠረት ለሌላ ድርጅት እንዲተላለፍ ይደረጋል።

፭/ የድርጅቱ የሒሳብ ማጣራት ሥራዎች ሲጠናቀቁ፣ በሒሳብ አጣሪው ጠያቂነት ኤጀንሲው ድርጅቱን ከመዝገብ ይሰርዛል።

፮/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ህብረቶች ወይም የህብረቶች ህብረት በሚፈርሱበት ጊዜ ቀሪ ንብረቶች ወደ አባል ድርጅቶች ወይም ህብረቶች ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡

3/ An organization which is dissolved in accordance with sub Article 1/A/ of this Article shall notify the Agency of the decision within fifteen days.

4/ The notification submitted to the Agency under sub article 3 shall be accompanied with the resolution to dissolve the organization, the currently activity report and statement of account of the organization.

**84/ Effects of Dissolution**

1/ Under sub article 83 once the dissolution of an organization is ordered, the property of the organization shall forthwith vest in the liquidator appointed by the Agency.

2/ The liquidator shall not perform any activities other than those necessary for its liquidation unless such activities are within the object of the organization and cannot be interrupted.

3/ Once the debts of the organization are paid and the costs of dissolution are settled, the liquidator shall affect the transfer of the remaining money or property to another organization in accordance with the Rules or a prior decision of the supreme body of the organization.

4/ If the rules or the decision of the Organization's supreme body do not provide for a recipient organization as per sub article 3 of this article, the remaining money or property shall be transferred to another organization designated by the Agency.

5/ After the liquidation process is concluded, the Agency shall cancel the name of the organization from its registry upon the request of liquidator.

6/ without prejudice to the provisions of this article when Consortiums or consorti of consortiums are Dissolved the remainning properties may be transferd to the member organizations or Consertiums.

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፹፭/ የድርጅቶች ምክር ቤት

፩/ በሁሉም ድርጅቶች ሙሉ ተሳትፎ የሚመራ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ ኤጀንሲው የምክር ቤቱን መሥራች ጉባዔ ይጠራል፣ ያስተባብራል።

፫/ ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች ይኖሩታል። ምክር ቤቱ የራሱን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል።

፬/ ድርጅቶች በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ የሚወከሉበት ስርዓት በምክር ቤቱ መመሪያ ይወሰናል።

፭/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከኤጀንሲው፣ ከለጋሾችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ዘርፉ ሊከተለው የሚገባውን የስነምግባር ደንብና ማስፈጸሚያ ስልት ያወጣል፣ አተገባበሩን በቅርበት ይከታተላል፣

ለ) በድርጅቶች ምዝገባና አስተዳደር ላይ ለኤጀንሲውና ለቦርዱ ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፣

ሐ) ዘርፉን ይወክላል፣ ያስተባብራል፣

፮/ ምክር ቤቱ በኤጀንሲው ቦርድ ውስጥ ድርጅቶችን የሚወክሉ ፫ ተወካዮችን ይመርጣል።

፯/ የምክር ቤቱ በጀት ከአባላት መዋጮና ከሌሎች ሕጋዊ ምንጮች ይሆናል።

፰/ ለምክር ቤቱ መመሥረትና መጠናከር ኤጀንሲው አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ያደርጋል።

## SECTION EIGHT

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 85/ Council of Civil Society Organizations

1/ A council governed by the full participation of all civil society organizations has been duly established by this Proclamation.

2/ The Agency shall convene and coordinate the founding meeting of the Council.

3/ The Council shall have a general assembly, executive committee and the necessary structures. The council shall enact its own internal rules.

4/ The procedures for representation of organizations in the general assembly of the Council shall be determined by the Directives of the Council.

5/ The council shall have the following powers and functions;

a) Enact the Code of Conduct for the sector, and devise enforcement mechanisms in consultation with the Agency, donors and other stakeholders,

b) Shall advise the Agency on the registration and administration of organizations,

c) Represent and coordinate the civil society sector.

6/ The council shall select three members of the Agency's board that will represent organizations.

7/ The source of the council's budget shall be member contributions and other legal means.

8/ The Agency shall extend the necessary cooperation for establishment and strengthening of the council.

**፹፮/ የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ**

፩/ በኤጀንሲው የሚተዳደር የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪/ የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ በጎ ፈቃደኝነትን እና የዘርፉን ዕድገት ለማበረታታት፣ በተለይም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚያገለግሉ ድርጅቶችን ለማበረታት ይውላል።

፫/ የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ ገቢውን የሚያገኘው፦

ሀ) ከዚህ አዋጅ በፊት ከፈረሱ ማኅበራትና ድርጅቶች የተገኘ በኤጀንሲው ይዞታ የሚገኝ ንብረት፣

ለ) በኤጀንሲው ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሚፈርሱ ድርጅቶች የሚገኝ ንብረት፣

ሐ) በመንግሥት ለፈንዱ የሚደረግ ድጎማ፣

፬/ ድርጅቶች ለሲቪል ማኅበረሰብ ፈንዱ መዋጮ ማድረግ አይችሉም።

፭/ የሲቪል ማኅበረሰብ ፈንድ አስተዳደርን በተመለከተ ኤጀንሲው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**፹፯/ የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ (አዋጅ ቁጥር ፩፻፷፮/፲፱፻፶፪) አንቀጽ ፳፭፣ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

፪/ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ልማድ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፹፰/ የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፰/፪ሺ፩፣ እንዲሁም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ያወጣቸው መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ

**86/ Civil Society Fund**

1/ A civil society fund administered by the Agency is hereby established.

2/ The civil society fund shall be used to encourage volunteerism and development in the sector, and provide incentives to organizations working with vulnerable groups.

3/ The income of Civil Society Fund shall come from:

a) Properties obtained from charities and societies dissolved before the enactment of this proclamation and are under the custody of the Agency;

b) properties obtained from organizations dissolved by the decision Agency or Court;

c) Subsidy from the Government to the Fund.

4/ Organizations may not contribute to the Civil Society Fund.

5/ The Agency shall issue Directives on the administration of the civil society fund.

**87/ Repealed and Inapplicable Laws**

1/ The Charities and Societies Proclamation No.621/2009, and Article 25 of the Commercial Code of Ethiopia (Proclamation No. 166/1960 are hereby repealed.

2/ Any law, Regulation, Directive and Customary Practice contrary to this Proclamation shall have no effect.

**88/ Transitory Provisions**

1/ The Charities and Societies Regulation No.168/2009 and directives issued by the Agency prior to the enactment of this Proclamation shall be for one year from the promulgation of this proclamation in the Federal Negarit Gazeta to the extent that they do not contravene with the provisions of this Proclamation.

አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ያህል ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪/ በአዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ መሠረት የተገኙ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን መሠረታዊውን መብቶችና ግዴታዎች እስካልተቃረኑ ድረስ ባሉበት ይቀጥላሉ።

፫/ በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ ለመሥራት ከሚመዘገቡ ድርጅቶች በስተቀር፣ በአዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ መሠረት የተመዘገቡ ድርጅቶች ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደገና በኤጀንሲው መመዝገብ አለባቸው።

፬/ በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የሚሰሩ ድርጅቶች አግባብነት ባለው የክልሉ መዝጋቢ አካል ይመዘገባሉ።

፭/ በአዋጅ ቁጥር ፮፻፳፩/፪ሺ፩ መሠረት የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ስልጣንና ተግባራት እንዲሁም መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ እንደተሻሻሉ ወደ ኤጀንሲው ይተላለፋሉ።

**፹፱/ ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ኤጀንሲው ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

2/ All rights and obligations created by Proclamation No. 621/2009 shall continue to exist insofar as they don't contravene with the fundamental rights and obligations provided for under this proclamation.

3/ All organization registered under Proclamation No. 621/2001 except those organizations operating in a single region shall register again within one year after the coming into force of this proclamation.

4/ All organizations operating in a single region shall be registered by the competent registrar of that region.

5/ Powers, duties, rights and obligation of the Charities and Societies Agency by proclamation No. 621/2009 as amended by this Proclamation shall be transferred to the Agency.

**89/ Power to Enact Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may enact regulations necessary to give effect to this Proclamation.

2/ The Agency may issue directives to give effect to this Proclamaiton and the Regulations enacted in accordance with sub Article 1 of this Article.

**፺/ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳሕለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**90/ Effective Date**

This Proclamation shall enter into force from the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**DONE AT ADDIS ABEBA, ON 7TH, DAY OF MARCH 2019**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**